*Haramaya Law Review, Vol.* 8 (2019) ISSN: 2227-2178 (P) & 2305-3739 (E)

**To cite this:** *አልዩ አባተ ይማም, (ምልከታ) የሸሪዓ እድገትና ቀዳሚ የሕግ ትምህርት ቤቶች፡ ከኢትዮጵያዊ ምልከታዎች ጋር*, HARAMAYA LAW REVIEW 8: 71-88 (2019)

# የሸሪዓ እድገትና ቀዳሚ የሕግ ትምህርት ቤቶች፡ ከኢትዮጵያዊ ምልከታዎች ጋር

*አልዩ አባተ ይማም**

## Abstract

*Ethiopian Sharia courts, which were given official status by Kadis Court Proclamation (1942) and Khadis and Naiba Councils Proclamation (1944), have been functioning in the country for more than half a century. Since this time, no modification has been introduced in the jurisdiction as well as in the structure of the courts. Moreover, with the adoption of the FDRE Constitution (Article 78(5), the status of Sharia courts has been made firm. Accordingly, a proclamation for the consolidation of Sharia courts was enacted in 1999 by the Federal parliament. As per the consolidation proclamation, the substantive law applicable on cases under the jurisdiction of Sharia courts is Islamic Law. The personal and family laws of Sharia and their general legal frameworks have been developed by two legal disciplines of Islam: Usul al-Fiqh (Islamic Jurisprudence) and Fiqh (Islamic law). These two fields of law are developed by the schools of law (Madhahib) of Sharia that have been evolving and contributing since the formative periods of Sharia law. This paper delves into the discussion of the salient features of schools of Sharia and their contribution in the formulation of Sharia principles of law and detail legal rulings in various fields of law including on personal and family matters. Further, the paper looks into the historical emergence of the Madhahib Sharia tradition in Ethiopia and its dissemination across various Muslim communities of Ethiopia since the 16$^{th}$ C. Ethiopian perspectives, in the sense that how the historical facts and developments of Madhhab are relevant to the interpretation and enforcement of the Sharia in Ethiopia to the extent it is allowed in the FDRE Constitution, are also indicated.*

### ሀ. መግቢያ

በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 34 እና 78 መሠረት የግልና የቤተሰብ ግጭቶች በባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ሕጎች መሠረት ሊዳኙ እንደሚችሉ እንዲሁም ሃይማታዊና የባህል ፍ/ቤቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በክልል ምክር ቤቶች እውቅና ሊሰጣቸውና ሊቋቋሙ እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡[1] በኢትዮጵያ የሕግ ብዝኃነት መድረክ ላይ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ መንግሥታዊ እውቅና አግኝተው

* ኤል.ኤል.ቢ፣ ኤል.ኤል.ኤም. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሕግ እጩ ዶክተር፣ ጸሐፊውን በኢ-ሜይል አድራሻ alyuabate09@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡

[1] የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 1፣ 1995 (ከዚህ በኋላ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት ይባላል)፣ አንቀጽ 34(5) እና 78(5)፡፡

ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ጎን ለጎን ሲሰሩ የነበሩት የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ብቻ እንደነበሩ የታወቀ ነው፡፡[2] ሆኖም የመጀመሪያውን ሕጋዊ እውቅና ያገኙት በ1934 በወጣው የቃዲ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1934 ነው፡፡ በኂላም በቃዲዎችና የናኢባ ምክር ቤቶች አዋጅ ቁጥር 62/1936 አማካይነት እንደገና ተደራጅተዋል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በፍ/ቤቶቹ አደረጃጀትም ሆነ በአሰራር ላይ ለውጥ ሳይደረግ በ1987 ዓ.ም የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ሲጸድቅ የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን ሕጋዊ አቋም ይበልጥ የሚያጠናክሩ አንቀጾች የሰነዱ አካል ተደረጉ፡፡ በዚህ ረገድ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ሕገ-መንግሥቱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰሩ የነበሩ በመሆኑ[3] ለፍ/ቤቶቹ እዉቅና መስጠትና ማደራጀት በፌዴራሉና በክልል ሕግ አዉጪ አካላት ላይ የተጣለ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ ተደርጓል፡፡[4] ባህላዊና ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶችን ማቋቋም በሕግ አውጪ አካላት ይሁንታ ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ከሕገ-መንግሥቱ መጽደቅ በፊት እውቅና የነበረው የዳኝነት አካል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ብቻ በመሆናቸው ሕልውናቸው በሕግ አውጪዎቹ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱ ራሱ እውቅና የሰጣቸው በመሆኑ[5] ወደፊት ከሚቋቋሙ ሌሎች የሃይማኖት ወይም የባህል ፍ/ቤቶች የተለየ ያደርጋቸዋል፡፡

የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም በተመለከተ በሕገ-መንግሥቱ የተጣለውን ግዴታ መሠረት በማድረግ የፌዴራሉና የክልል መንግሥታት የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም የሚያጠናክሩ አዋጆች *(Consolidation Proclamations)* አውጥተዋል፡፡[6] በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤት ማጠናከሪያ አዋጅ አንቀጽ 4 መሠረት የሸሪዓ ሕግ ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚቀርቡ የግልና የቤተሰብ ጉዳዮችን ለመፍታት ይተገበራል፡፡ ሸሪዓ ሲባል ሁለት የሕግ ክፍሎችን ሊወክል ይችላል፤ *አሱል አል-ፊቅሕና ፊቅሕ*፡፡ *ኡሱል አል-ፊቅሕ* ለዝርዝር የሸሪዓ ሕግጋት መሠረት የሆኑ ጥቅል የሕግ መርሆዎችን የሚመለከትና የሚያጠና የእውቀት መስክ ሲሆን *ፊቅሕ* ደግሞ በልዩ ልዩ የሰው ግለሰባዊና ማህበራዊ እንዲሁም ሃገራዊ ጉዳዮችን የሚገዙ ዝርዝር ሕግጋትን የሚመለከት የጥናት ዘርፍ ነዉ፡፡[7] እነዚህ ሁለት የኢስላም የሕግ ሳይንሶች የረጅም ዘመናት የምርምርና ሥነ-ጽሁፍ እድገት ያላቸዉ ሲሆን በዓለም ዙሪያ ባሉ የሙስሊም ሃገራት ውስጥ በተለያየ ደረጃ ተፈጻሚ ሲደረጉ የነበሩና በመደረግ ላያ ያሉ በመሆኑ በንድፈ-ሐሳብ ደረጃም ሆነ ተጨባጭ ሕብረተሰባዊ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ጥልቅና የዳበረ የእውቀትና የተሞክሮ አሻራ አላቸው፡፡[8]

ሸሪዓ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት በተፈቀደው የተፈጻሚነት ወሰን ውስጥ በመሆን ለግልና የቤተሰብ ዝርዝር ሕግጋት አረዳድና አተገባበር መሪ መርሆዎችን በ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* አማካይነት ይዘረጋል፡፡ ዝርዝር ድንጋጌዎችን በተመለከተ ቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች በሆኑት በቁርአንና *ሱናሕ*[9] ውስጥ በተካተቱት

---

[2] Mohammed Abdo, *Legal Pluralism, Sharia Courts, and Constitutional Issues in Ethiopia*, 5(1) MIZAN LAW REVIEW, 78 (Spring 2011). ዛኪ ሙስጠፋ፣ *በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የእስላም ፍርድ ቤቶች የሚሰራበት ሕግ፤ ለሸሪዓ ሕግ በሥራ ላይ መዋልና መቀጠል ምክንያት የሆኑ ነገሮች*፣ 9(1) JOURNAL OF ETHIOPIAN LAWS፣ 173(1965)፡፡

[3] *የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ፣* ቁጥር 188/1992፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ 6ኛ ዓመት ቁጥር 10፣ መግቢያ፡፡

[4] የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት፣ 78(5)፡፡

[5] ዝኒ ከማሁ

[6] በፌዴራሉ ፓርላማ የወጣው የሸሪዓ ፍ/ቤቶች አዋጅ፣ የፍርድ ቤቶቹን አቋም ለማጠናከር የወጣ እንጂ ማቋቋሚያ አዋጅ እንዳልሆነ ከአዋጁ አጭር ርዕስ (አንቀጽ 1)፣ ‹‹የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን *አቋም ለማጠናከር* የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992›› መረዳት ይቻላል፡፡

[7] MOHAMMAD HASHIM KAMALI, SHARIA LAW: AN INTRODUCTION 40-41 (Oxford፡Oneworld Publications, Oxford, 2008).

[8] MOHAMMAD HASHIM KAMALI, PRINCIPLES OF ISLAMIC JURISPRUDENCE, xi-xvii (Cambridge፡The Islamic Texts Society, 1991).

[9] ቁርአንና *ሱናሕ* በመለኮታዊ ራዕይ የተገለጹ መለኮታዊ የሸሪዓ ምንጮች ሲሆኑ ቁርአን በቃሉም ሆነ በሐሳቡ ፍጹም መለኮታዊ የሆነ የፈጣሪ ቃል ሲሆን ሱናሕ ደግሞ የመጨረሻውን የአምላክ ነቢይ የሙሀመድ ኢብን ዓብዲላሕ ንግግሮችና

*ጥቅል የሕግ መርሆዎችና ልዩ ድንጋጌዎች ላይ በመመርኮዝ በቀደምትና በዘመኑ የሸሪዓ ሊቃውንት የተለያየ አተረጓጎም ሲሰጣቸው ቆይቷል። የሕግ አረዳድ ልዩነት (ኢኽቲላፍ) ከሸሪዓ አነሳስ ጀምሮ በግለሰብ ሊቃውንትና በቡድን (መዛሒብ) ደረጃ ሲንጸባረቅ የኖረ አይነተኛ የሸሪዓ መገለጫ ነው።*[10]

*በኢትዮጵያ ሸሪዓ ፍ/ቤት እየቀረቡ ያሉ የቤተሰብና የግል ግጭቶችን ለመፍታት ተፈጻሚ የሚደረጉትን የሸሪዓ ሕግ መርሆዎችና ዝርዝር የቤተሰብ ሕግጋትን ከማጥናት በፊት የእነዚህን የጥናት መስኮች ታሪካዊ ዳራ ማወቅ መርሆዎቹንና ድንጋጌዎቹን በተገቢው መንገድ ለመረዳትና ለመፈጸም አስፈላጊ ነው። በተቃራኒው የሸሪዓን ጠቅላላ እድገት፣ የሕግ ት/ቤቶች ሊመሠረቱና ሊዳብሩ የቻሉበት ዓላማና የርስ-በርስ ግንኙነት አለመገንዘብ በመዛሒብ አማካይነት የዳበሩትን የግልና የቤተሰብ የሥረ-ነገር ሸሪዓዊ ድንጋጌዎች በተሳሳተ አረዳድ ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያደርግ አብይ ምክንያት ነው።*[11] *ስለሆነም ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ ከሸሪዓ ሕግ ጥንስስ ጀምሮ ታሪካዊ የእድገት እርከኖችን እንዲሁም ለዚህ እድገት የሕግ ት/ቤቶችና የቀደምት የሸሪዓ ሊቃውንት የነበራቸውን ምሁራዊ አበርክቶ በማስቃኘት በዚህ ረገድ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የታሪክ ግንዛቤ የመፍጠር ዓላማ ያለው ሲሆን በሸሪዓ እድገት ታሪክ ሒደት ለተፈጠረው መዝሓባዊ ብዝሓነት ሊሰጠው የሚገባውን ሚዛናዊ አተያይ ያመላክታል። በዚህ ረገድ ጥናቱ ሸሪዓ እድገት ታሪክ ጥናት (ታሪኽ አት-ተሽሪዕ) ምሁራዊ ተዓማኒነትና ቅቡልነት ያላቸውን ድርሳናት መሠረት ያደረገ ሲሆን ለርዕሰ ጉዳዩ ኢትዮጵያዊ ገጽታዎች ደግሞ ‹በኢስላምና ሙስሊሞች በኢትዮጵያ ጥናት› ታላቅ ምሁራዊ አሻራ ያላቸውን እንደ ሁሴን አህመድ ያሉ አጥኚዎች ያዘጋጇቸውን የታሪክና የሥነ-ማህበረሰብ ምርምር ውጤቶችን ያገናዘበ ነው።*

*ይህ ጽኁፍ ይህን የመግቢያ ክፍል ጨምሮ በአጠቃላይ በስድስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን ተከታዩ ሁለተኛ ክፍል ሸሪዓ ከጥንስሱ ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ ያለፈባቸውን አምስት የእድገት ደረጃዎች የሚዳስስ ሲሆን አንዱ ደረጃ ከሌላው የሚለይባቸው የለውጥ ኩነቶችም ተገልፀዋል። በሦስተኛው ክፍል ሥር ለሸሪዓ ሕግ መዳበር የጎላ ድርሻ ያላቸውን መዛሒብ ጠቅላላ መገለጫዎችና ለእድገቱ ያላቸው አስተዋጽኦ ሲዳሰስ በሸሪዓ ሕግ ት/ቤቶች መካከል ያሉ የጋራ አቋሞችና የልዩነት ነጥቦች በአራተኛው ክፍል ስር ተለይተዋል። አምስተኛው ክፍል ደግሞ ከጠቅላላው የመዝሓብ እድገት ታሪክ በተለየ የሕግ ት/ቤቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ወደ ተለያዩ የሃገሪቱ ሙስሊሞች ሕብረተሰቦች የነበራቸውን ሥርጭትና የተከሉትን የሸሪዓ ትምህርት ባህል በጥቅሉ ያስቃኛል። በመጨረሻም በጽኁፉ ውስጥ የተነሱ አብይ ሐሳቦች ተጠቃለው የቀረቡበት የማጠቃለያ ክፍል ሥድስተኛውን ክፍል ይይዛል።*

## *ለ. የመጀመሪያዎቹ አምስት የፊቅሕ እድገት ደረጃዎች*

*በነቢዩ ሙሀመድ እድሜ የመጨረሻዎቹ* 23 *ዓመታት* (610-32 *ዓመተ-ልደት*(ዓ.ል)/እ.አ.አ) *የቁርአን ራዕይ መውረዱን ተከትሎ የአማኞችን ባህሪና ሥነ-ምግባር የሚመሩ ሕግጋት መውረድና በነቢዩ በኩል በራዕይ ሲገለጹ የነበሩ የሱናሕ ድንጋጌዎችና ማብራሪያዎች የመጀመሪያውን የሸሪዓ እድገት ጥንስስ ጥለዋል።*[12] *ሕግ ነክ የቁርአን ድንጋጌዎች የወረዱት በዋናነት በመዲና ነበር። ሆኖም የወቅቱ ሙስሊም ማሕበረሰብ ዋነኛ ትኩረት የነበረው የቁርአንን መልዕክት መረዳት በመሆኑና ቁርአን ደግሞ ከጥቂት ዝርዝር ሕግጋት በስተቀር እጅግ ሰፊው ክፍል በእምነትና አመለካከት ላይ ያተኮረ ስለሆነ የማሕበረሰቡም ትኩረት ይህንኑ የተከተለ ነበር።*[13] *መለኮታዊ ሕጎች ይወርዱ የነበረው በግለሰብ*

---

*ተግባራትን የሚወክል ቃል ነው። የነቢዩ ሙሀመድን ንግግሮችና ተግባራት የተላለፉባቸው ዘገባዎች ደግሞ ሀዲስ (አሃዲስ) ይባላሉ።* KAMALI, PRINCIPLES, *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ* 14-44።

[10] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, *ገጽ*. 9.

[11] *ዝኒ ከማሁ ገጽ* 10.

[12] *ዝኒ ከማሁ ገጽ* 246.

[13] *ዝኒ ከማሁ*

ወይም በሕብረተሰብ ደረጃ ይነሱ የነበሩ ጥያቄዎችንና ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት እንጂ በንድፍ-ሐሳብ ደረጃ ያሉና በተጨባጭ ያላገጠሙትን ለመግዛት ጭምር አልነበረም፤[14] ስለሆነም ይነሱ ለነበሩ ጥያቄዎች ቀጥተኛ *ራዕያዊ (የወህይ)* ምላሽ ይሰጥ የነበረ በመሆኑ ግላዊ የሕግ አስተያየትና ንድፈ-ሐሳባዊ *ኢጅቲሓድ* አስፈላጊ አልነበረም፡፡[15]

ሁለተኛው *የፊቅሕ* እድገት ከነቢዩ ሕልፈት በኋላ ያለውን የሙስሊም ግዛት በተመረጡ ቅን አመራሮች ሲተዳደር የነበረበትን ጊዜ (632-661 ዓ.ል) የሚመለከት ነው፡፡[16] በነቢዩ የሕይወት ዘመን ባልተነሱ አዳዲስ ጭብጦች ላይ ቀድሞ በቁርአንና በ*ሱናሕ* አስተምህሮት የተተከለዉን የሕግ ውጥን በማስፋፋት ለአዳዲስ ችግሮችና ጥያቄዎች መፍትሔ የሚሆን የሕግ ምርምርና አስተያየት ይሰጥ ነበር፡፡ በዚህም በግል አስተያየት ላይ የተመረኮዘ *ፊቅሕ* የሚዳብርበትን መሠረት ጥሏል፡፡[17] የነቢዩ ባልደረቦች ለቁርአንና *ሱናሕ* ሕጎች ምክንያታዊ አቀራረብ ያላቸው ሲሆን ከቋንቋዊ ትርጉም ይልቅ ሕጉ ሊያሳካው ያሰበውን ዓላማ ያገናዘበ አተረጓጎም ይከተሉ ነበር፡፡ የባልደረቦቹ የሕግ አረዳድ ከሌሎች የሸሪዓ ሊቃውንት አስተያየት በተለየ የአስገዳጅነት ደረጃ እንዳለው የሚቆጠረውም የነቢዩ አስተምኅሮት ቀጥተኛ ወራሾች በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ዘመን ከታየው በተሻለ የሕጉን ዓላማ ያማከለና የሕጉን ዓላማ እውን የሚያደርግ የሕግ አተረጓጎም የተከተሉ መሆኑ ስለሚታመንበት ነው፡፡[18]

*ሦስተኛዉ* የሸሪዓ እድገት ደረጃ የተከታዮች *(ታቢዑን)* ዘመን በመባል የሚታወቀውና ሁለት ታላላቅ የእሳቤ ጎራዎች የተፈጠሩበት ጊዜ ሲሆን የኡመያድ *ሥርወ-መንግሥት ሥልጣን* ከያዘ ጀምር እስከ አገዛዙ ማብቂያ ያለውን ጊዜ (661-750 ዓ.ል) የሚሸፍን ነው፡፡[19] አንደኛው የእሳቤ ጎራ መቀመጫውን በመካሕና በመዲና (ሒጃዝ) አድርጎ የነበረው *የሀዲስ* ተከታዮች *(አሕል አል-ሀዲስ)* የእሳቤና የሕግ ት/ቤት ሲሆን የዚህ ቡድን ሊቃውንት የሚደርሱባቸው የሕግ ድምዳሜዎች ሁሉ ከነቢዩና ከባልደረቦቻቸው የተገኙ ዘገባዎችን የተንተራሱ ሲሆን በምክንያታዊ አስተሳሰብ ላይ ለሚገነቡ ግላዊ የሕግ ምልከታዎች ሸሪዓዊ የአስረጂነት ዋጋ አይሰጡም ነበር፡፡[20] ሁለተኛው ጎራ ደግሞ በዒራቅ በስራና ኩፋ ከተሞች የተመሠረተው የአመክንዮ ተከታዮች *(አሕል አር-ረኢይ)* የእሳቤ ቡድን ሲሆን ከአምልካዊ ድንጋጌዎች በስተቀር የሸሪዓ ሕጎች በጠቅላላው የተደነገጉበት የየራሳቸው ምክንያትና ዓላማ አላቸው በሚል እሳቤ የተመሰረተ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ የሕግ ሊቅ *(ሙጅተሒድ)* የድንጋጌዎቹን ምክንያት በመመርመር የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች ለሕጎቹ አተረጓጎምና ለአዳዲስ ጭብጦች እልባት ለመስጠት መንደርደሪያ ሊያደርጋቸው ይገባል የሚል አቋም አላቸው፡፡[21] ከፖለቲካ አመራርነት ጋር በተያያዙ አለመግባባቶች ምክንያት ሺዓ የሚል መጠሪያ ያገኘው ቡድንም ከዋናው የሙስሊም ሕብረተሰብ የተገነጠለውና በኋላም የሺዓ የሕግ እሳቤ ክፍል የተመሠረተው በዚሁ ዘመን ነበር፡፡[22] በአጠቃላይ

---

[14] ዝኒ ከማሁ

[15] ዝኒ ከማሁ

[16] ከነቢዩ ሙሀመድ ሕልፈት በኋላ የግዛት አስተዳደሩን ተረክበው በቅንነት ያገለገሉት ተተኪ አመራሮች *(ኸለፋእ አር-ራሺዱን)* የሚባሉት አቡ-በክር አስ-ሲዲቅ ዑመር ኢብን አል-ኸጧብ ዑስማን ኢብን ዐፋንና ዐሊ ኢብን አቢ ጧሊብ ናቸው፡፡ እነዚህ የነቢዩ ባልደረቦች በአስተዳዳሪነት ጊዜያቸው ያጋጠማቸው ፈጣንና ተለዋዋጭ ፖለቲካዊና ወታደራዊ እውነታ ተጋፍጠው በተጓዳኝ ለሚነሱ የ*ፊቅሕ* ጥያቄዎችና ግጭቶች በጋራና በግለሰብ ደረጃ *ኢጅቲሓድ* በማድረግ የደረሱባቸው የሕግ አተረጓጎሞችና ድምዳሜዎች የነቢዩ ሙሀመድ አስተምኅሮት ነጸብራቅ እንደሆኑና አስገዳጅ እንደሆኑ ብዙኃኑ የሸሪዓ ሊቃውንት የሚጋሩት አቋም ነው፡፡ (KAMALI, PRINCIPLES, *ግርጌ ማስታወሻ* 8፣ *ገጽ* 236-243 ይመለከቷል፡፡)

[17] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, *ገጽ*. 246-247.

[18] ዝኒ ከማሁ ገጽ 247

[19] ዝኒ ከማሁ

[20] ዝኒ ከማሁ

[21] ዝኒ ከማሁ

[22] ዝኒ ከማሁ ገጽ 247-248.

የነዚህ የሕግ እሳቤ ጎራዎች መመስረት ከእነሱ በኋላ ለመጣው ሰፊ *የፊቅሕ* እድገት መሠረት የጣለና ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳረፈ ሆኗል።[23]

አራተኛው የሸሪዓ እድገት የአመክንዮአዊ የምርምር ዘመን (750-950 ዓ.ል) በሚል የሚታወቅ ሲሆን *ፊቅሕ* የላቀ እድገት ያሳየበትና ዘመናትን ተሻግረው ተጽእኖ መፍጠር የቻሉ *መዝሓቦች* የተፈጠሩበትና ሰፊ የሕግ መርሆዎችና ዝርዝር ሕግጋት ከቁርአንና ከሱናሕ የተቀሰሙበትና የተተነተኑበት ዘመን ነበር።[24]

አምስተኛው የእድገት ደረጃ ከአባሲድና ከኡቶማን ሥርዓት መውደቅ ጀመሮ ዘመነኛው *የኢጅቲሓድ* ንቅናቄ እስከተጀመረበት 20ኛው ም.ል መጀመሪያ ድረስ ያለውን ጊዜ የሚሸፍን ሲሆን በነዚህ ጊዜያት የምዕራብ ቅኝ-ገዢዎች የሙስሊም ግዛቱን በመቆጣጠር በሸሪዓ ሕግ ፍልስፍና ምትክ የራሳቸውን የሕግና የፍትሕ ሥርዓት በሃገራቱ ላይ ጭነውባቸዋል። በዚህም ምክንያት ሸሪዓ የሕብረተሰቡን ሕይወት ከመምራትና በጀመረው የእድገት ጎዳና ላይ ከመራመድ ይልቅ ቀድሞ በሥነ-ጽሑፍና በቃል የተላለፈውን *የፊቅሕ የኢጅቲሓድና የመዛሒብ* እውቀት በማጥናትና በማብራራት ላይ የተገደበ እንዲሆንና የመዝሓቦችን የሕግ ምልከታዎች የሙጥኝ በማለት አዳዲስ የሕግ ምልከታዎች የማይበረታታበት ሁኔታ ነገሰ።[25] ከሸሪዓ ነባራዊነትና ተለማጭነት ባህሪ ጋር በማይጣጣም መልኩ የጭፍን ተከታይነት *(ተቅሊድ)* ቡድናዊነትና የአንጃዊነት እሳቤዎች ሥር ሰደው ከ10ኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ ጀምሮ የዓለም ሙስሊም ማሕበረሰብ አይነተኛ መገለጫ ሆኖ ቆይቷል። ለዘጠኝ ምዕተ-ዓመታት የዘለቀው ይህ እውነታ *የፊቅሕ* እድገት በነበረበት እንዲገታና ሸሪዓ በየወቅቱ ለሚቀያየረው የማሕበረሰብ ተጨባጭ እውነታና ፍላጎት ምላሽ መስጠት እንዳይችል አድርጎታል።[26] የቀደሙት *የመዛሒብ* አቋሞች በንድፈ-ሐሳባዊ የሕግ ማብራሪያ ሥራዎች ላይ ብቻ የተንጸባረቁበትና ከማሕበራዊ እውነታ ጋር ያላቸው ተዛምዶ የተቋረጠበት ዘመናት ሆነው ተመዝግበዋል።[27]

## ሐ. የሸሪዓ ሕግ ት/ቤቶች (*መዝሓቦች*)

*መዝሓብ* ማለት በአንድ ራሱን ችሎ የሕግ ምርምር የማድረግ ችሎታ ባለዉ ሊቅ የሚመራ ከሌሎች መዝሓቦች የሚለይበት የራሱ የሕግ ንድፈ-ሐሳቦችና አቀራረቦች ያሉትና ተከታዮችን ማፍራት የቻለ የሕግ እሳቤ ክፍል ነው።[28] *መዝሓቡ* በዋናው ኢማም ከተቋቋመና ዋና ዋና የሕግ መርሆዎች ከተቀረጹ በኋላ እነዚህን መርሆዎች በመተንተንና በማብራራት ረገድ የመሪው ተማሪዎችና ተከታዮች ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። *መዝሓብ* በአንድ ወይም በተለያየ ዘመናት በሚመጡ ምሁራን የሥነ-ጽሑፍ ቅብብሎሽ እየበለጸገ መጥቶ በእድገቱ አንድ የተለየ የሕግ እውቀት ማዕቀፍ ያለው ነው።[29] *መዝሓቦች* ‹‹የሕግ ት/ቤት›› የተባሉበትም ምክንያት ዋነኛ የምርምር ትኩረታቸው ከመንፈሳዊ ጉዳዮች ይልቅ በሕግ ላይ በመሆኑና *በመዛሒብ* መካከል ያለውም ዋነኛ ልዩነት በሕግ ጉዳዮች ላይ በመሆኑ ነው። መሠረታዊ የእምነት ጉዳዮችን በተመለከተ *በመዝሓቦች* መካከል ልዩነት የለም። በርግጥ በዝርዝር እምነት ጉዳች

---

[23] KAMALI, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 248

[24] ዝኒ ከማሁ

[25] ዝኒ ከማሁ

[26] ዝኒ ከማሁ

[27] ዝኒ ከማሁ ገጽ 249

[28] Khalifa Babikr Al-Hassan, *Religious Schools of Law*. in The Different Aspects Of Islamic Culture, Vol. 6, Part II, 19 (UNESCO, 2016).

[29] MUHAMMAD HASHIM KAMALI, THE ENCYCLOPEDIA OF RELIGION, 66 (New York: Macmillan Publishing, 1987).

ላይ በምሁራን መካከል ሰፊና ውስብስብ ልዩነቶች ቢኖሩም እነዚህ የልዩነት መስመሮች በመስኩ *ሥነ-ጽሑፍ* ውስጥ የ*መዝሓብ* ተብለው አይጠቀሱም፡፡[30]

ከላይ እንድተመለከተው የ*መዝሓቦች* አመሠራረት ታሪክ ሲታይ ኢስላማዊ ትምህርትና ምርምር የሚደረግባቸው ሁለት ማዕከላት በዒራቅና በሒጃዝ መቋቋም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በማዕከላቱ ከነበሩ የ*ፊቅሕ* መምህራን መካከል ተጽእኖ ፈጣሪ የነበሩት ወጥተው በጉልህ ተለይተው የወጡት የሕግ እሳቤ ት/ቤቶች የሐሳቦቹ ባለቤት በሆኑት ሊቃውንት *ሥም* መጠራት ጀመሩ፡፡[31] የሕግ እሳቤ ክፍሎቹ ሁለት መሠረታዊ የአቀራረብ ልዩነቶች ነበራቸው፡፡ አንደኛው የሒጃዝ ቡድን ለሚይዟቸው የሕግ አቋሞች ሁሉ ከነቢዩ በተላለፉ ዘገባዎች ላይ የሚደገፉ ነበሩ፡፡[32] የዒራቁ ክፍል ደግሞ ከነቢዩ ይተላለፉ ለነበሩ የ*ሀዲስ* ዘገባዎች የነበራቸው ተደራሽነት እንደ መዲናዎች ስላልነበርና ከአመክንዮኣዊ አስተሳሰብ አኳያ ለአጠራጣሪ ዘገባዎች አነስተኛ ዋጋ ስለሰጡ ለአዳዲስ የሕግ ጭብጦች ሸሪዓዊ እልባት ለመስጠት በዋናነት በአመክንዮ ላይ ይመረኮዙ ነበር፡፡

1. *የሀነፊ መዝሓብ*

የዚህ መዝሓብ *መሥራች* አቡ-ሀኒፋ ኑዕማን ኢብን ሳቢት ናቸው፡፡ አቡ-ሀኒፋና መዝሓባቸው ከተጨባጭ የሕግ ጉዳዮች ይልቅ በንድፈ-ሐሳባዊ የሕግ ጥያቄዎች ላይ የማተኮር እንዲሁም በ*ረእይ* (ግላዊ አተያይ) እና በ*ቂያስ* (ምስስሏዊ አመክንዮ/*analogical reasoning)* ላይ የመመርኮዝ ከፍተኛ ዝንባሌ አላቸው፡፡[33] አቡ-ሀኒፋ በንግድ ስራ የተሰማሩ ስለነበር በንግድ ግብይቶች ዙሪያ በሚነሱ የሕግ ጉዳዮች ላይ *ኢጅቲሓድ* በማድረግ በዚህ ረገድ ላለው የሸሪዓ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡[34] አቡ-ሀኒፋ የመዝሓባቸውን መርሆዎች በመቅረጽ ሂደት ላይ ለግለሰቦች መብትና ነጻነት ከፍ ያለ ዋጋ የሰጡ ሲሆን አሳማኝ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በግለሰብ መብትና ነጻነት ላይ ዘፈቀዳዊ ገደብ በማስቀመጥ አያምኑም፡፡ ለምሳሌ ያህል የሴቶችን መብት በተመለከተ አንዲት አካለ-መጠን የደረሰች ሴት ያለሞግዚት ፈቃድ ጋብቻ የመፈጸም ሸሪዓዊ መብቷን ያረጋግጣሉ፡፡[35] አካለ-መጠን የደረሰች ሴት ንብረቷን የማስተዳደር ሙሉ መብትና አቅም እንዳላት ቁርአን እስካረጋገጠ ድረስ በጋብቻ ዙሪያ ላይም ቢሆን ዉሳኔ የመስጠት አቅም ላይኖራት አይችልም ይላሉ፡፡[36]

ከአቡ-ሀኒፋ ንግግሮች መካከል የታወቀውና በሌሎች *መዛሕብ* መሪዎችና ተከታዮች ሰፊ ተቀባይነት ያገኘዉ ‹‹*ኢዛ ሶለሃ አል-ሀዲስ፣ ፈሑወ መዝሓቢ* (የአንድ *ሀዲስ* ተዓማኒነት የተረጋገጠ ከሆነ መዝሓቤ (አቋሜ) ነው)›› የሚለው ተራማጅ ንግግራቸው በወቅቱና በኋላ የተፈጠሩት መዝሓቦች የነበራቸው የ*ሀዲስ* ተደራሽነት ውስን የነበረና መጠነ-ሰፊ የ*ሀዲስ* አሰባሰብ *ሥራ* ያልተከናወነ መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ንግግር ነበር፡፡ የመዝሓባቸው ተከታዮች በዚህ መርህ መሰረት ቀደም ሲል የአቡ-ሀኒፋ ወይም ተቀዳሚ ተማሪዎቻቸው የ*ኡሱል* መርሆዎችና የ*ፊቅሕ* ድንጋጌዎች በኋላ ከተገኙ ተዓማኒ *ሀዲሶች* ጋር የሚቃረኑ ከሆኑ ሀዲሱን ቢያዉቁ ኖሮ መርሆው ወይም ድንጋጌው ላይ አይደረሱም ነበር በሚል እሳቤ የአቋም ማስተካከያዎችን አድርገዋል፡፡[37]

ሌላው የአቡ-ሀኒፋ መዝሓብ መሪ ቃል ‹‹ማንም ሰው አስረጂ ምንጩን እስካላወቀ ድረስ በኛ *መዝሓብ* ላይ ተመርኩዞ *ፈትዋ* (የሕግ ብይን) ሊሰጥ አይችልም›› የሚለው ሲሆን ጭፍን ተከታዮች እንደሚሉት ሳይሆን በ*መዝሓብ* መሪዎችና በቀዳሚ ምሁራን እይታ ሳይገደቡ በየወቅቱ የሚነሱ

---

[30] ዝኒ ከማሁ.
[31] ዝኒ ከማሁ.
[32] ዝኒ ከማሁ.
[33] ዝኒ ከማሁ.
[34] ዝኒ ከማሁ.
[35] ዝኒ ከማሁ ገጽ 70-71.
[36] ዝኒ ከማሁ.
[37] ዝኒ ከማሁ ገጽ 71.

ሊቃውንት አካባቢያዊ እውነታዎችን በማገናዘብ አዲስ ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ንግግር ነው፡፡[38] የፊቅሕ ሕግጋት መገኛ ምንጭ የተደነገጉበት መንስኤና ዓላማን መለየት ከተቻለ ሕጎቹ ለየወቅቱ ያላቸውን ተገቢነት በመመዘን ከሙተቀዲሙን የፊቅሕ እይታዎች የተለዩ የኢጅቲሓድ ድምዳሜዎች ላይ መድረስ ይቻላል፡፡[39]

*ሙቀሊዱንና የመዝሓብ* ወገንተኝነት ያለባቸው ኂለኛ የሀነፊ ሊቃውንት እንደሚሉት ከ*ሙተኣኺሩን* መካከል *ሙጅተሒድ* ሊባል የሚችል የሕግ ምሁር የሌለ በመሆኑ በቀደምት *የመዝሓብ* መስራቾች መካከል ያሉ ልዩነቶችን ከምንጮች አኳያ በመፈተሽ ምርጫ ማድረግ ስለማይቻል *የመዝሓቡ* ፈር ቀዳጆች እንደ ቅደም-ተከተላቸው ሊመረጡ ይገባል እስከ ማለት ደርሰዋል፡፡[40] እንደ አቡ-ሱለይማንና ዐልዋኒ ያሉ የዘመኑ የሸሪዓ ሊቆች እንደሚያስረዱት የዚህ አይነቱ ጭፍን የሕግ እሳቤ ቁርአንና *ሱናሕን ለመዝሓቦች* ተገዢ ከማድረግ የማይተናነስና የዘመኑን ትውልድ ለእሳቤ ቀወስ *(Crisis of Thought)* የዳረገ ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡[41] የእሳቤ ቀውስ ከአምላክ መጽኃፍና ከነቢዩ *ሱናሕ* ጋር ቀጥተኛ ትስስር ካለመፍጠርና ነጻ አስተሳሰብ ከሌለው ወግ አጥባቂነት የመነጨ አሳሳቢ ችግር እንደሆነ ዐልዋኒ ያስገነዝባሉ፡፡[42]

የሀነፊ *መዝሓብ* በ16ኛው ም.ዓ በኦቶማን ቱርኮች ዘመን ባገኘው ተቀባይነትና ሰፊ *ሥርጭት* ምክንያት ከሌሎቹ መዝሓበች በበለጠ ባሁኑ ጊዜ በቱርክ በሶሪያ በዮርዳኖስ በሊባኖስ በፓኪስታን በአፍጋኒስታንና በሕንድ በስፋት ተግባራዊ የሚደረግና በአጠቃላይም ከዓለም ሙስሊም ማሕበረሰብ ሲሶው የሀነፊ *መዝሓብ* ተከታይ ነው፡፡[43]

## 2. የማሊኪ *መዝሓብ*

ይህ መዝሓብ የተመሠረተው የመዲና ከተማ ዳኛና የሕግ አማካሪ በነበሩት በማሊክ ኢብን አነስ አል-አስባሒ ነው፡፡[44] ማሊክ በሌሎች መዝሓቦችና ኢማሞች እንደ አስረጅ ያልተወሰደ ‹የመዲና ነዋሪዎች ተግባር ወይም ልማድ *(ዓመል አሕል አል-መዲና)* የተሰኘ የሸሪዓ አመክንዮኣዊ መርሆ ነድፈዋል፡፡ የመርሆው መነሻ ሐሳብ የመዲና ነዋሪዎች በነቂስ ይተገብሩትና ያምኑበት የነበረ ድርጊትና አሰራር ከጥንትም ከሙሀመድና ባልደረቦቹ አስተምህሮት ተቀስሞ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ቢሆን ነው ከሚል ግምት የመነጨ ነው፡፡[45] የማሊኪ *መዝሓብ* ዋነኛ ዋቢ የሆነው በአሰድ አል-ፉራት የተጠናቀረው ‹*አል-ሙዳወናሕ አል-ኩብራ* (ታላቁ ጥንቅር)› የተሰኘው መጽሐፍ ነው፡፡ መዝሓቡ በአሁኑ ወቅት በሞሮኮ አልጀሪያ ቱኒዚያ የላይኛዉ ግብጽ ሱዳን ባህሬንና ኩዌት ሰፊ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡[46]

ኢማም ማሊክ የመዲና ነዋሪዎች ተግባር ወይም ልማድ በተጨማሪ ቀድመው ከተለዩት የኢጅቲሓድ መርሆዎች ላይ የመዲና ነዋሪዎች ወጥ አቋም *(ኢጅማዕ አሕል አል-መዲናሕ)* *ኢሰቲስላሕ* (የሕዝብ ጥቅም)ና *ሰድ አዝ-ዘራኢዕ* (ከምንጩ ማድረቅ) የተሰኙ የሕግ ንድፈ-ሐሳቦችን አክለዋል፡፡ ማሊክ ራሳቸው ከለዩኣቸው የሕግ መላምቶች በተጨማሪ ሌሎች *የመዛሒብ* ሊቃውንት የደረሱባቸውን

---

[38] ዝኒ ከማሁ ገጽ 72
[39] ዝኒ ከማሁ
[40] ዝኒ ከማሁ
[41] Taha Jabir Alwani, *The Crisis of Thought and Ijtihad*, 10(2) AMERICAN JOURNAL OF ISLAMIC SOCIAL SCIENCES, 234 (1993).
[42] ዝኒ ከማሁ
[43] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 73
[44] KAMALI, THE ENCYCOLPEDIA OF RELIGION, *supra* note 25, p. 67
[45] Khalifa, *supra* note 24, p. 30
[46] KAMALI, THE ENCYCOLPEDIA OF RELIGION, *supra* note 25, p. 68

መርሆዎች ተቀብለው የመዝኃባቸው አካል በማድረጋቸው መዝሐቡ ከየትኛውም *መዝሐብ* በላይ እጅግ ሰፊና የአቃፊነት ባህሪ ያለው እንደሆነ ከማሊ ይገልጻሉ፡፡[47]

የሕዝብ ጥቅም ሐሳብን ያፈለቁት ማሊኪ ባይሆኑም መርሆው በምንም ቅድመ-ሁኔታ ሳይታሰር ራሱን የቻለ የሕግ ምርምር ምንጭ እንዲሆንና ሰፊ ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረግ ቀዳሚና ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉ በመሆኑ ኢስቲስላሕ የማሊኪ ጭማሬ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ለምሳሌ የሕብረተሰቡን ሰላምና መረጋጋት ለመጠበቅ ሲባል ዝቅተኛ ድምጽ ያገኘው እጩ እንዲመረጥና የሃገር መሪ እንዲሆን ቢደረግ ተገቢ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህ የከፋ ጉዳትን በመከላከል *(ደፍእ አድ-ዶረር)* ላይ የተመሠረተ እሳቤ ከኢስቲስላሕ ሐሳብ የመነጨ መሆኑን ይገነዘቧል፡፡[48]

ማሊክ ከነጠላ *(አሀድ)* የ*ሀዲስ* ዘገባ (በአንድ ወይም በጥቂት የዘገባ መስመሮች ብቻ የተላለፈ *ሀዲስ)* ይልቅ ለየባልደረቦችና ለመዲኖች የጋራ ተግባር የበለጠ የአስረጅነት ዋጋ ይሰጣሉ፡፡ ለምሳሌ ተዋዋዮች በአካል እስካሉ ድረስ የፈጸሙትን ውል ማፍረስ እንደሚችሉ የሚገልጸውን *አሃድ ሀዲስ* አይቀበሉቱም ምክንያቱም በመዲኖች ተግባር መሠረት ውል ከተፈጸመ በኋላ የተዋዋዮቹ አብሮነት ለውሉ ማፍረሻ በቂ ምክንያት አይሆንም፡፡[49] ሻፊዒ በበኩላቸው የመዲና ማሕበረሰብ ልማድ ከ*ሀዲስ* ጋር መስማማት ይገባዋል እንጂ የሕብረተሰቡ ተግባር ከነቢዩ አስተምህሮት የመጣ ነው በሚል መላምት *ሀዲሱን* አለመቀበል ተገቢ አይደለም የሚል ትችት ሰንዝረዋል፡፡[50] በተጨማሪም ማሊክ የመዲናዎችን ወጥ አሠራር መሠረት በማድረግ ባሏ ያልተገባ አያያዝ እንደሚይዛት *(ዶረር)* ያስረዳች ሚስት ፍቺ መጠየቅ ትችላለች የሚል አስተያየት አላቸው፡፡ ሌሎቹ *መዝሐቦች* በዚህ ጉዳይ ፍርድ ቤት ባልየውን መቅጣት እንጂ ፍቺ መወሰን አይችልም የሚል አቋም ይዘዋል፡፡[51] ከቤተሰብ ጉዳይ ሳንወጣ ሚስት በጋራ ሥምምነት ፍቺ እንዲፈጸም በምትጠይቅበት *ሥነ-ሥርዓት (ኹል)* የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት መብት ያለው ባል ነው፡፡ እንደ ማሊኪ እይታ ደግሞ ነገሩ በፍርድ ሊወሰን እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡[52] በእነዚህና መሰል ጉዳዮች ላይ ማሊኪዎች ያንጸባረቋቸው አቋሞች ባለንበት ዘመን በመካከለኛው ምስራቅና በኤስያ የሚገኙ በርካታ ሙስሊም ሃገሮች የቤተሰብ ሕግ ማሻሻያዎቻቸው አካል አድርገዋቸዋል፡፡[53]

የመዝሐቡን ከምንጩ ማድረቅ ንድፈ-ሐሳብ ምንነት በአጭሩ ለማየት ያህል ግዴታን *(ዋጂብ)* ለመፈጸም የሚያስፈልግ ሁሉ *ዋጂብ* ነው፤ ወደ ክልክል *(ሀራም)* የሚያደርስ ሁሉ የክልከላው አካል ነው የሚል ሐሳብ ያዘለ ነው፡፡ በተመሳሳይ *ሀላልን* (የተፈቀደን) ለማከናወን የሚያስፈልግ ሁሉ ያስፈላጊነቱን ያህል *ሀላል* ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በጦርነት ጊዜ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ማድረግ ወይም ለአልኮል (ወይን) ጠማቂ የወይን ፍሬ መሸጥ ወይም ወደ ወለድ *(ሪባ)* የሚያስገባ ማንኛዉም ውል ሁሉም ውጤታቸው *ሀራም* በመሆኑ መንስኤዎቻቸውም ክልክል ይሆናሉ፡፡[54] የማሊኪ ሊቅ የሆነው አል-ቀራፊ እንደገለጸው የማሊኪ እሳቤ የሆነው ከምንጩ ማድረቅ በሁሉም መዝሐቦች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ የሕግ ጽንሰ-ሐሳብ ነው፡፡[55]

ባጠቃላይ ኢማም ማሊክ በ*ሀዲስ* መስክ ብቻ ሳይሆን የፊቅሕ መሠረቶችን *(ኡሱል)* በማዳበር ረገድ ከመሪ ኢማሞች ተርታ የሚሰለፉ ናቸው፡፡ ጭፍን የሕግ ተከታይነትንም እርሳቸውና መዝሐባቸው እንደ ሌሎቹ ሁሉ የከረረ ነቀፌታ ሰንዝረውበታል፡፡ በዐባሲድ ዘመነ-መንግሥት መሪ የነበረው አል-መንሱር

---

[47] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 75
[48] ዝኒ ከማሁ
[49] ዝኒ ከማሁ ገጽ 74
[50] ዝኒ ከማሁ
[51] ዝኒ ከማሁ ገጽ 75-76
[52] ዝኒ ከማሁ ገጽ 76
[53] ዝኒ ከማሁ
[54] ዝኒ ከማሁ
[55] ዝኒ ከማሁ ገጽ 77

የማሊክ የ*ሀዲስ* ጥንቅር የሆነው *አል-ሙወጦእ* የግዛቱ ብቸኛ *መመሪያ* እንዲሆን ሐሳብ አቅርቦላቸው ይህ በነቢዩ ባልደረቦች ጊዜ ከነበረው የ*ኢጅቲሓድ* ብዝኃነትና የመቻቻል የሕግ ባህል ጋር የሚጣረስና ፈጠራዊ የእሳቤ ነጻነት እንዲነጥፍ የሚያደርግ ነው በማለት ሐሳቡን አልተቀበሉትም፡፡[56]

### 3. የሻፊዒ *መዝሐብ*

እስካለንበት ዘመን ደርሰው ሰፊ ተቀባይነት ካገኙ ት/ቤቶች መካከል የሻፊዒ *መዝሐብ* አንዱ ነው፡፡[57] *መዝሐቡ* በታችኛው ግብጽ ደቡብ አረቢያ ምስራቅ አፍሪካ ኢንዶኔዥያ ማሌዥያና ብሩናይ (Brunei) በስፋት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን በፍልስጤም ዮርዳኖስና በሶሪያም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተከታይ ማፍራት ችሏል፡፡[58] *መዝሐቡ* የማሊክ ተማሪ በሆኑት በሙሀመድ ኢብን ኢድሪስ አሽ-ሻፊዒ የሕግ ቀኖናዎች ላይ የተመሰረተ ሲሆን መስራቹ አራት የሸሪዓ ምንጮችን ማለትም ቁርአን *ሱናሕ ኢጅማዕና ቂያስ* በሚል ቅደም-ተከተል ያስቀመጡ የመጀመሪያዉ የ*ኡሱል* ተመራማሪ ናቸው፡፡[59] ሻፊዒ የሸሪዓ ምንጮችን የእርስ-በርስ ትስስር የሀነፊንና የመምህራቸውን የማሊኪን የሕግ ንድፈ-ሐሳቦች ጽኑእነት በመመርመር የማይስማሙባቸውን ነጥቦች በማስረዳትና የ*ኡሱል* መርሆዎችን በአንድነት በማጠናቀር *‹አር-ሪሳላሕ›* በተሰኘው ድርሳናቸው ወጥ የ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* ትንታኔ ያቀረቡ በመሆናቸው *‹የኡሱል አባት›* የሚል መጠሪያ ተሰጥቷቸለዋል፡፡[60] የሕግ አቀራረብ ዘዴዎችን *(Methodology of Law)* የቀደሙት የ*ኡሱል* አጥኚዎች በጨረፍታ ያነሷቸው ቢሆንም አጠቃላይ የሸሪዓ ሕግ መዋቅሩን በመንደፍና የምንጮችንና የአስረጂዎችን የእርስ-በርስ ዝምድና የበላይነትና የበታችነት የመሳሰሉ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ አጽንዖት በመስጠት ሰፊ ዳሰሳ ያደረጉት ኢማም አሽ-ሻፊዒ ናቸው፡፡[61]

በተጨማሪም አሽ-ሻፊዒ እንደ *ዐም* (ጥቅል) እና *ኻስ* (ልዩ) ሻሪ *(ናሲኽ)* እና ተሻሪ *(መንሱኽ)* በመሳሰሉ የሕግ አተረጓጎሞች ላይ ማብራሪያ በማቅረብ የመጀመሪያው ናቸው፡፡[62] አሽ-ሻፊዒ የጨመሯቸው አዳዲስ ጽንሰ-ሐሳቦችና ማብራሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው በኢስላም የሕግ እድገት ውስጥ ያላቸው ዋነኛ ሚና ቀድመው በ*አሱል ሥነ-ጽሑፍ* የተዳሰሱ ንድፈ-ሐሳቦችንና ምልከታዎችን ማጥናት በማይስማሙባቸው መርሆዎችና አቀራረቦች ላይ የከረሩ ሂሶችን በመሰንዘር መስኩ ወደፊት የሚያድገበትን አቅጣጫዎች የተለሙ ናቸው፡፡[63] ለምሳሌ ያህል ሻፊዒ ያለፉት የ*ኡሱል* ኢማሞች ለ*ሀዲስ* የነበራቸው አቋም ላይ የጠበቀ ሂስ ሰንዝረዋል፡፡ አቡ-ሀኒፋ በአንድ የዘገባ ሠንሠለት ብቻ የተላለፈ ዘገባ ይልቅ ለአመክንዮ ቅድሚያ መስጠታቸው ኢማም ማሊክ ደግሞ ከ*አሃድ* ዘገባዎች ይልቅ ለ*ዐመል አሕል አል-መዲና* ቅድሚያ መስጠታቸውን በጥብቅ ነቅፈዋል፡፡ በሌላ አገላለጽ ለ*ሀዲስ* የሚሰጡት የአስረጅነት ዋጋ ከሌሎች በበለጠ እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡[64]

በ*ኢጅማዕ* ጽንሰ-ሓሳብ ላይ ሻፊዒ የያዙት ግንዛቤ ከአቡ-ሀኒፋና ማሊክ የተለየ ነው፡፡ *ኢጅማዕ* እንደ ሻፊዒ ከሆነ የማሕበረሰቡ ወጥ አቋም ማለት ነው፡፡ የምሁራን የጋራ አቋም ነው የሚለው የአቡ-ሀኒፋና የማሊኪ ትርጓሜ በተጨባጭ ከዚህ በፊት እውን ሊሆን ያልቻለ ወደፊትም ሊሳካ የሚችልበት እድል የተመናመነ በመሆኑ ለ*ኢጅማዕ* ጠበብ ያለ ትርጉም መስጠትን መርጠዋል፡፡[65] ያም ሆኖ ከሻፊዒ በኋላ

---

[56] ዝኒ ከማሁ
[57] KAMALI, THE ENCYCOLPEDIA OF RELIGION, *supra* note 25, p. 68
[58] ዝኒ ከማሁ፡፡
[59] ዝኒ ከማሁ፡፡
[60] ዝኒ ከማሁ፡፡
[61] KAMALI, SHARIA LAW, *supra ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 78
[62] ዝኒ ከማሁ፡፡
[63] COULSON, NOEL J., A HISTORY OF ISLAMIC LAW, 53 (Edinburgh University Press, 1971)::
[64] KAMALI, THE ENCYCOLPEDIA OF RELIGION, *supra* note 25, p. 68
[65] ዝኒ ከማሁ፡፡

በታየው የሸሪዓ እሳቤ እድገት የኢጅማዕ እይታቸው ተቀልብሶ በሀነፊና ማሊክ የኢጅማዕ ትርጓሜ እንዲተካ ሆኗል፡፡[66]

በቁርአንና በሱናሕ መካከል ያለውን ትስስር በተመለከተ የቀደምት የመዝሓብ ባለቤቶች ቁርአን ሱናሕን ወይም በተቃራኒው ሱናሕ ቁርአንን ሊሽር እንደሚችል ቢገልጹም ሻፊዒ ግን ይህን እይታ ውድቅ በማድረግ ሱናሕ በቁርአን ያልተሸፈነ አዲስ ሕግ የሚቀርጽበት ሁኔታ ቢኖርም ዋነኛ ሚናው ቁርአንን ማብራራት በመሆኑ ቁርአንን ሊሽር አይችልም የሚል አተያይ አላቸው፡፡[67]

የሸሪዓ ምንጮች ሲባል ቁርአንና ሱናሕ ወይም ከእነዚህ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆን አለበት የሚል እሳቤ ካላቸው ሊቃውንት የመጀመሪያው አሽ-ሻፊዒ ናቸው፡፡[68] ለማንኛውም የሕግ ጥያቄ ምላሽ መጀመሪያ ከቁርአንና ከሱናሕ መፈለግ ይኖርበታል፡፡[69] ጭብጡ በቀጥታ ያልተሸፈነ ከሆነ ከእነዚህ ምንጮች ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለውና የሕጎችን ምክንያት *(ዒላሕ/ratio legis)* እና ዓላማዎች ተራዝሞ ለአዲሱ ጭብጥ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚደረግበት ‹ምስስሏዊ አመክንዮ› ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ለሻፊዒ ከቁርአንና ሱናሕ ቀጥሎ ምንጭ ሊሆን የሚችለው የኢጅቲሓድ መርሆ ቂያስ ብቻ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ለሻፊዒ ኢጅቲሓድ ማለት ቂያስ ማለት ነው፡፡[70] በዚህም መሠረት በሌሎች ኢማሞች የተለዩት የኢጅቲሓድ መርሆዎች ከምንጮች በጣም የራቁ ናቸው በሚል አይቀበሏቸውም፡፡ ለምሳሌ የማሊኪ ‹የሕዝብ ጥቅም› እና የሀነፊ ሐሳብ የሆነውን ‹ኢስቲህሳን (ርትዕ)› አልተቀበሏቸውም፡፡[71] ቂያስ ከቁርአንና ከሱናሕ ጋር ምክንያተ-ሕግ የሚጋራ በመሆኑ ከምንጮቹ እምብዛም አይርቀም፡፡ ሌሎቹ መርሆዎች ከምንጮች ጋር ያላቸው ትስስር የላላና በግል እይታ ላይ በእጅጉ የተመረኮዙ በመሆኑ ዘፈቀዳዊ ባህርይ ያላቸው ናቸው በሚል እሳቤ በሻፊዒ ዘንድ የአስረጅነት ዋጋ የላቸውም፡፡[72]

ከሱናሕ አስረጅነት ጋር በተያያዘ የሀዲስ ዘገባዎች ከኢጅቲሓድ መርሆዎች ጋር በተጋጩ ጊዜ ተገቢነታቸው አጠያያቂ በሆኑ የሀዲስ ተዓማኒነት ምዘና መስፈርቶች መሠረት ዘገባዎቹ ወደጎን ሲደረጉ የነበሩበት የቀደምት መዛሒብ አካሄድ ትክክል አይደለም በሚል ሻፊዒ ተችተዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሀዲስ በአንድ ወይም በጥቂት አስተላላፊዎች ብቻ ወርዶ መዘገቡ ብቻ ኢ-ተዓማኒ አያደርገውም፡፡ ምክንያቱም ሙሀመድ በነቢይነት ደረጃቸው ከብዙኃኑ ምዕመናን ጋር ብቻ ሳይሆን ከግለሰቦችና ከጥቂት ሰዎች ጋርም ግንኙነት የነበራቸውና በእነዚህ ግንኙነቶች ወቅት አምላካዊ መመሪያዎችን ያስተላለፉ በመሆኑ ኣሀድ ዘገባዎችን ውድቅ ማድረግ ተገቢነት የለውም፡፡[73] በአንድ ዘገባ ብቻ መተለላፉ ጥርጣሬ ቢፈጥርም ከመጀመሪያው የሙስሊም ትዉልድ በኋላ የመጣው ተተኪ ትውልድ የእነዚህን ዘገባዎች ተዓማኒነት ማረጋገጥና የእርስ-በርስ ተደጋጋፊነታቸውን መሠረት በማድረግ ተዓማኒነታቸውን መመዘን ሲችል እንዲሁ በጠቅላላው አስረጅ አይሆኑም ማለት ተገቢነት የለውም ይላሉ፡፡[74] እንደ እምነትና አምልኮ ባሉ በአመክንዮኣዊ ምርምር ምላሽ ሊያገኙ የማይችሉ ጉዳዮች በኣሀድ ዘገባዎች ሽፋን አግኝተው ሳለ ኣሀድ ሀዲሶች አስረጂነት የላቸውም ማለት ሃይማኖቱን ለመረዳትና ለመተግበር ወሳኝ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ የመመሪያ እጦት እንዲፈጠር የሚያደርግ መሆኑን ሻፊዒ አክለው ያሳሳባሉ፡፡[75]

---

[66] ዝኒ ከማሁ፡፡

[67] KAMALI, SHARIA LAW, ግርጌ ማስታወሻ 7, p. 78

[68] Ahmad Hasan, *The Sources of "Fiqh": A General Survey*, 29 (2) ISLAMIC STUDIES, 111 (1990).

[69] KAMALI, THE ENCYCOLPEDIA OF RELIGION, *supra* note 25, p. 68. በቁርአን የሸሪዓ ሕግ ምንጭነት ላይ፣ አልዩ አባተ፣ ‹ቀዳሚዉ የሸሪዓ ሕግ ምንጭ - ቁርኣን› 2 HAWASSA UNIVERSITY JOURNAL OF LAW, 123-153 (2018) ያንብቡ

[70] KAMALI, ዝኒ ከማሁ

[71] Ahmad, *The Sources of "Fiqh"*, *supra* note 63, p. 112.

[72] KAMALI, SHARIA LAW, *supra* note 7, p. 78

[73] ዝኒ ከማሁ

[74] ዝኒ ከማሁ

[75] ዝኒ ከማሁ

እዚህ ላይ ግልጽ ሊሆን የሚገባው የሀነፊና የማሊኪ *መዝሓቦች* ከሀዲሳዊ ምንጮች ይልቅ ለአመክንዮአዊ የሕግ መርሆዎች ከፍ ያለ የአስረጂነት ደረጃ የመስጠት አዝማሚያ ያሳዩት *ሱናሕ* ከአመክንዮአዊ እሳቤዎች በላይ አስገዳጅ የሸሪዓ ምንጭ መሆኑን ባለመቀበል ሳይሆን የ*መዝሓቦቹ* መርሆዎች በተቀረጹበት ወቅት ከነቢዩ *ሙሀመድ* ተላለፉ የተባሉ የ*ሀዲስ* ዘገባዎች በስፋት ያልተሰበሰቡና ያልተጠናቀሩ በመሆናቸውና የ*ሀዲሶች* ተዓማኒነት የሚመዘንባቸው መስፈርቶች ገና ያልበለጸጉ ስለነበር በቂ ምዘና ማድረግ ባለመቻሉ ነው፡፡[76] በተጨማሪም *መዝሓቦቹ* በተጠነሰሱበት ወቅት *ሀዲስ* በዋናነት አካባቢያዊ ባህሪ የነበረውና በአንድ አካባቢ የሚታወቅ *ሀዲስ* ካለ ጥቅም ላይ ሊውል ካልሆነም በምትኩ *ኢጅቲሓድ* የሚደረግበት አካሄድ ሰፍኖ የነበረ በመሆኑ የወቅቱ የ*ሑሱል ሊቃውንት* ለ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎቻቸው ከፍ ያለ ሚና መስጠታቸው ሁኔታው የሚያስገድድና አማራጭ በማጣታቸው ምክንያት እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡[77] ሻፊዒ የተነሱበት ጊዜ ሐሰተኛ የ*ሀዲስ* ዘገባዎች በመበራከታቸው በየአካባቢው ይነገሩ የነበሩ *ሀዲሶች* በስፋት የተሰበሰቡበትና የተጠናቀሩበት ወቅት በመሆኑ ለአከራካሪ የሕግ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጡ ተዓማኒ *ሀዲሶች* ማግኘት የሚቻል ስለሆነና ተዓማኒ *ሀዲሶችን* መለያ የሆኑ የምዘና ዘዴዎች በወቅቱ ዳብረው የነበረ በመሆኑ በሻፊዒ ዘመን ከ*ኢጅቲሓድ* ይልቅ *ሀዲስን* ቅድሚያ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚቻልበት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡[78]

በመጨረሻም *ተቅሊድን* በተመለከተ ሻፊዒ እንደ ሌሎች ሁሉ የከረረ ነቀፌታ ሰንዝረዋል፡፡ ስለ *ሙቀሊዶች* በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው ንግግራቸው ‹‹ያለ አስረጅ እውቀትን የሚፈልግ በጨለማ እንጨት እንደሚለቅም ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው እንጨት ነው ብሎ እባብ ይዞ እንደተነደፈ ሰው አይነት ነው፡፡››[79] ያሉት ነው፡፡ የ*ሙተቀዲሙን* የሕግ መርሆዎችና የደረሱባቸው ዝርዝር የሕግ ድምዳሜዎች ዕልፍ ዓመት ተሻግረው ለአሁኑ ዘመን ሙስሊም ማሕበረሰብ አግባብነት አላቸው አይሻሻሉም አይለወጡም እንዲሁም *ኢጅቲሓድ* ማድረግ የሚችል የለም የሚል የጭፍን ተከታይነትና የወግ አጥባቂነት ዝንባሌ ነው፡፡

## 4. የሀንበሊ *መዝሓብ*

የ*ሀዲስ* አስረጂነት ከፍ እንዲል የሻፊዒን አሻራ ያስቀጠሉና ያጠናከሩ ሁለት አዳዲስ *መዝሓቦች* በ9ኛው ም.ል ተመስርተዋል፡፡ እነሱም አሁን የማይገኘውና በዳውድ አዝ-ዟሒሪ የተመሠረተው የዟሒሪ *መዝሓብ* እና በአህመድ ኢብን-ሀንበል የተመሰረተው የሀንበሊ *መዝሓቦች* ናቸው፡፡[80] ኢብን ሀንበል ከሌሎቹ *መዝሓቦች* በኋላ ሰፊ የ*ሀዲስ* ጥንቅርና ተደራሽነት በነበረበት ወቅት በመምጣታቸው የ*ፊቅሕ* ጥያቄዎችን ከ*ኢጅቲሓድ* ይልቅ በ*ሀዲስ* አማካይነት የመፍታት እድል ነበራቸው፡፡ *በኢጅቲሓድ* ላይ የከረረ ሂስ ይሰነዝሩ ስለነበር በታቻለ መጠን አመክንዮአዊ የ*ፊቅሕ* ምርምርን ተግራዊ ላለማድረግ ይጥሩ ነበር፡፡[81] እንደ *ቂያስ*ና *መስላሃሕ* ባሉ የ*ኢጅቲሓድ* አስረጂዎችን በስሱ ብቻ ይጠቀሙ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ኢብን ሀንበልና ተከታዮቻቸው እንደ *ፉቀሓእ* (የሕግ ሊቃውንት) ሳይሆን እንደ *ሀዲስ* ሰብሳቢዎችና ተንታኞች *(Traditionalists)* ብቻ ተደርገው ይታዩ ነበር፡፡[82] ከ14ኛው ምዕተ-ዓመት በኋላ የዚህ *መዝሓብ* *ሥርጭት*ና ተቀባይነት በተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች እያሽቆለቆለ ቢመጣም በ18ኛው ም.ዓ በአረቢያ ባህረ-ሰላጤ የተንሰራፋው የወሓቢያ ንቅናቄ ተነሳሽነቱንና መርሆዎቹን የወሰደው ከሀንበሊዎች

---

[76] Ahmad Hasan, *Origins of the Early Schools of Law: The Historical Background*, 9(3) ISLAMIC STUDIES, 264-265 (1970).

[77] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 80.

[78] ዝኒ ከማሁ.

[79] ዝኒ ከማሁ.

[80] ዝኒ ከማሁ.

[81] ዝኒ ከማሁ.

[82] KAMALI, THE ENCYCOLPEDIA OF RELIGION, *supra* note 25, p. 68.

በመሆኑ *መዝሓቡ* እንደገና ሊያንሰራራ ችሏል። ባለንበት ዘመንም በሳውዲ አረቢያ ሰፊ ተቀባይነት ያለው ሲሆን በኦማን በኳታር በባህሬንና ኩዌት ብዙ ተከታዮች አሉት።[83]

ኢብን ሀንበል ከባልደረቦች የሕግ አስተያየት ይልቅ የተዓማኒነት ደረጃው ደካማ ቢሆንም ለ*ሀዲስ* ቅድሚያ ይሰጡ ነበር። ለምሳሌ ለተፈታች ሚስት ቀለብ መቁረጥን አስመልክቶ ዑመር ኢብን አል-ኸጧብ እንዲከፈል የሚያዘውን *ሀዲስ* ደካማ *(ዶዒፍ)* ሆኖ በማግኘታቸው ቀለብ እንዲቆረጥ ያዘዙ ቢሆንም ይህን የባልደረባ *ፈትዋ* ኢብን-ሀንበል አልተቀበሉትም። አስረጂነቱ አጠያያቂ ቢሆንም *ሀዲሱን* መሠረት አድርገው የቀድሞ ባል ለፈታት ሚስቱ ቀለብ የመክፍል ግዴታ የለበትም የሚል አቋም አንጸባርቀዋል።[84]

ሌላዉ የሀንበሊ *መዝሓብ* መገለጫ ከሌሎቹ *መዝሓቦች* በተለየ ለ*ኢባሃሕ* (ፍቁድ) የሕግ ቅርጽ የጎላ ሚና እንዲኖረው አድርገው የሚተረጉሙ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ውል የማድረግ ነጻነትን በተመለከተ ሌሎቹ በተለያየ ደረጃ የውል ነጻነትን የሚገድቡ ቅድመ-ሁኔታዎች በማስቀመጥ የስምምነቱ ጽኑነት በእነዚህ መስፈርቶች መሠረት እንዲወሰን የሚያደርጉ ቢሆንም የሀንበሊዎች እይታ *ዒባዳት* (የአምልኮ ሕግጋትን) በተመለከተ መርሁ በሕግ ከተቀመጠው የአምልኮ *ሥነ-ሥርዓት* ውጪ በግል ነጻነት ወይም በስምምነት መጨመር ወይም መቀነስ አይቻልም የሚል ቢሆንም ውሎችንና ግብይቶችን በተመለከተ ግን መርኁ ፍቁድነት ነው። በሌላ አነጋገር በሸሪዓ ግልጽ ክልከላ እንዳለ እስካልተረጋገጠ ድረስ የውል ፍሬ-ነገሮች ለተዋዋዮች ስምምነት የተተው ናቸው ማለት ነው። በቁርአን ላይ የተመለከተውም ውሎች በተዋዋዮች ነጻ ፈቃድ መፈጸም እንዳለባቸው[85] እና ከስምምነት በኋላ የገቡትን ቃል ማክበር እንዳለባቸው ብቻ ነው።[86] ነገሩን በአንድ ልዩ ምሳሌ ግልጽ ለማድረግ ያህል ከአንድ በላይ እስከ አራት ማግባት በሸሪዓ ግዴታ ሳይሆን የተፈቀደ በመሆኑ ጋብቻ የፈጸመ ባል ሌላ ሚስት ላለማግባት ከሚስቱ ጋር ውል ሊገባ ይችላል። ሌሎቹ መዝሓቦችና ብዙኃኑ ሊቃውንት ደግሞ ከአንድ በላይ ማግባት ሸሪዓ የፈቀደው በመሆኑ በውል መገደብ አይቻልም የሚል አቋም ይዘዋል።[87]

*ተቅሊድን* በተመለከተ ዋናው *ኢማምና* በየዘመናቱ የተተኩት የሀንበሊ *ዑለማእ* በጠቅላላ *ተቅሊድን* ያወገዙ ሲሆን በምትኩ ችሎታው ያለው ሁሉ *ኢጅቲሓድ* እንዲያደርግ ያበረታቱ ነበር። *ሙጅተሒዶች* እንዲፈጠሩና *ኢጅቲሓድ* ማድረግ የየማሕበረሰቡ የወል ግዴታ *(ፈርድ ከፋኢ)* እንደመሆኑ በየትኛውም ዘመንና ማሕበረሰብ ውስጥ *ኢጅቲሓድ* ሳይቋረጥ የሸሪዓውን ቀጣይነትና ተለማጭነት ማረጋገጥ እንዳለበት የሀንበሊ ሊቃውንትም በጥብቅ ያሳስባሉ።[88]

## 5. የሺዓ መዝሓቦች

‹ሺዓ› የሚለው ቃል በአራተኛው የ*ኺላፋ* አመራር ዘመን መሪ የነበረውን ዐሊ ኢብን ጧሊብን ለመከተል ከብዙኃኑ የሙስሊም ማህበረሰብ የተለየ የሙስሊም የፖለቲካ ርዕዮት ይዘው የነበሩ ቡድኖችን ለማመልከት የሚውል ሲሆን ይህ ርዕዮት *ኢማሚያ* በመባል ይታወቃል።[89] በ*ኢማምያ* እሳቤ መሠረት አምላክ ነቢይን ከላከና ነቢያዊ ተልዕኮ ዘመን ካበቃ በኋላ የሙስሊም ማህበረሰቡንና ግዛቱን አመራር በተመለከተ ለሕብረተሰቡ ዘፈቀዳዊ ውሳኔ ሊተወው አይችልም። ይልቁንም በነቢይ የተመረጡ አመራሮችን ይሰይማል። ይህ አጠቃላይ መለኮታዊ ባህል ከነቢዩ ሙሀመድ ሕልፈት በኋላም ተግባራዊ መደረግ ያለበት ሲሆን በሺዓ ነቢያዊ ዘገባ እንደተረጋገጠው ከዐሊ ኢብን አቢ-ጧሊብና የነቢዩ ልጅ

---

[83] ዝኒ ከማሁ ገጽ 84.
[84] ዝኒ ከማሁ.
[85] ቁርአን፣ 4፡19.
[86] ቁርአን፣ 5፡1.
[87] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 86.
[88] ዝኒ ከማሁ ገጽ 85.
[89] ANWAR AHMAD QADRI, SLAMIC JURISPRUDENCE IN THE MODERN WORLD, 159 (New Delhi, Taj Company, 1997).

ከሆነችው ከባለቤቱ ፋጢማ ቢንት ሙሀመድ የዘር ሐረግ የተገኙ ተወላጆች ለሕዝበ-ሙስሊሙ የተመረጡ እጩ አመራሮች ናቸው የሚል እሳቤ አላቸው።[90]

ከሺዓ *መዝሓቦች* መካከል ሌሎቹ ጠፍተው ‹*ኢስና ዐሸርያ* (አስራ-ሁለትዮሽ)› ዘይዲና ኢስማዒሊ ብቻ ቀርተዋል።[91] ልዩነታቸው ከአራተኛው የዘር ሐረግ በኋላ ባሉት ተተኪ አመራሮች ማንነት ላይ ሲሆን እስከ አራተኛው ማለትም ከዐሊ ኢብን ጧሊብ አል-ሀሰን (የዐሊ ልጅ) አል-ሁሰይን (የሁለተኛው የዐሊ ልጅ) እሰከ ዐሊ ዘይን አል-ዐቢዲን (የሁሴን ልጅ) ድረስ አንድ አይነት ተወራራሽ ዘውዳዊ ሥርዓትን ይከተላሉ።[92] *ኢስና ዐሸሪያ* እስከ አስራ-ሁለተኛው የዘር ሐረግ ድረስ ያሉ ተወራራሽ ተወላጆችን በኢማምነት የተቀበሉ ሲሆን ይህ *መዝሓብ* የብዙኃኑን የሺዓ ማሕበረሰብ ተከታይነት ማግኘት ችሏል።[93] ከአሥራ-ሁለቱ አመራሮች መካከል ሰባቱን ብቻ የሚቀበሉት ደግሞ ኢስማዒሊያዎች ሲሆኑ *ሰብዒያ* (ባለሰባትዮሽ) እየተባሉ ይጠራሉ።[94] ልዩነቱ የተፈጠረባቸው የዘር ሐረግ እርከኖች ሁለት ሲሆኑ ዐሊ ዘይን አል-ዐቢዲን ሲሞት ከፊሉ የሺዒ ተከታይ ለልጃቸው ለዘይድ ተከታይ ሲሆን እርሱም የዘይዲያ ሺዓ መስራች ሆነ። ሌሎቹ ደግሞ ለሌላኛው የዐሊ ልጅ ለሙሀመድ አል-ባቂር ተከታይ ሆኑ። በዚህም ምክንያት ከዋነኛው የሺዓ ግንድ *ዘይዲያ* የሚባል ቅርንጫፍ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል።[95] ሌላው ልዩነት የተፈጠረበት የሥልጣን ርክክብ እርከን ጀዕፈር አስ-ሷዲቅ ከታላቁ ልጁ ከኢስማዒል ይልቅ ሙሳ አል-ካዚምን በአመራርነት ሰይሞ ሲሞት እዚህ ላይ በተከታዮች ዘንድ ሁለት ጎራ እንዲፈጠር ምክንያት ሆነ። ታላቁን ወንድም ኢስማዒልን የኢማሚያ ሥርዓቱ ተተኪ አድርገው የተቀበሉት ‹ኢስማዒልያ› ይባላሉ። ነገር ግን ብዙኃኑ የሺዓ ሕዝበ-ሙስሊም የተቀበለው የሙሳ አል-ካዚምን *ኢማምነት* ነው። በዚህ ልዩነት የተነሳ ከዋናው የሺዓ አመራር የዘር-ሐረግ ተዋረድ ተገንጥሎ ‹ኢስማዒሊያ› የተባለ ሌላ የሺዓ *መዝሓብ* ሊፈጠር ችሏል።[96]

የሺዒ ሥርዓት ጀዕፈር አስ-ሷዲቅ በ*ኢማምነት* እስከተሰየመበት ጊዜ ድረስ በዋናነት ፖለቲካዊ ገጽታ የነበረው ነው። በመሆኑም በሥልጣን ሽግግር ላይ ትኩረት የሚሰጥና የራሱ የሆነ ልዩ የሕግ እሳቤዎች የሌለው ነበር። ከጀዕፈር አስ-ሷዲቅና ከሙሀመድ አል-ባቂር በኋላ ልዩ የሕግ እሳቤዎችንና አቀራረቦችን በማዳበር የራሱን የ*መዝሓብ* ቅርጽ ሊይዝ ችሏል። በተለይ የሺዓ *መዝሓብን* በማዳበር ረገድ ፈር ቀዳጅ የሆኑት ሙሀመድ አል-ባቂር ናቸው።[97] እንደ ሸሪዓ *መዝሓብ* ከሌሎች የሕግ ት/ቤቶች አንጻር ልዩነቱ የመጣው በሱኒ የሸሪዓ *መዝሓቦች* ውስጥ የነቢዩ ሙሀመድ ባልደረቦች በተለይም አመራር የነበሩት የአቡ-በክርና የዑመር ኢብን አል-ኸጧብ የሕግ ብይኖች በሱኒ ማሕበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ የአስረጅነት ደረጃ ያላቸውን ያህል በሺዓ ዘንድ ምንም አይነት የአስረጅነት ፋይዳ የማይሰጣቸው መሆኑ ነው።[98] በተጨማሪም ከላይ እንደተገለጸው የሊቃውንት ወጥ አቋም በባልደረቦች ዘንድ ከፍተኛ ፋይዳ የነበረውና በሱኒ የ*ኡሱል* ሊቃውንት ዘንድ ከቁርአንና ከሱናሕ በመቀጠል ሦስተኛ የአስረጂነት ደረጃ ያለው ሲሆን በሺዓ *መዝሓብ* አተያይ ደግሞ የተለየ ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጓል። ይኸውም *ኢጅማዕ* ከተባለ የ*ኢማሞች* ወጥ አቋምን የሚመለከት መሆኑ ነው።[99]

---

[90] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 88.
[91] ዝኒ ከማሁ.
[92] ዝኒ ከማሁ ገጽ 87.
[93] ዝኒ ከማሁ.
[94] ዝኒ ከማሁ ገጽ 88.
[95] ዝኒ ከማሁ.
[96] ዝኒ ከማሁ ገጽ 87-88.
[97] KAMALI, SHARIA LAW, *supra* note 7, p. 89.
[98] ዝኒ ከማሁ.
[99] ዝኒ ከማሁ ገጽ 89-90.

*የሀዲስን* አስረጅነት በተመለከተ ‹*ሥድስቱን ተዓማኒ የሀዲስ* ስብስቦችን *(አል-ሲሃሕ አል-ሲታሕ)*› የማይቀበሉና በአምስት የሺዒ *የሀዲስ* ስብስቦች ተተክተዋል:: እነሱም *አል-ካፊ፣ መን-ላየስተህዚሩሑ አል-ፈቂሕ፣ ተሕዚብ፣ ኢስቲብሷርና ነሕጅ አል-በላጋ* ናቸው፡፡[100] ለሱኒ ተዓማኒ *የሀዲስ* ስብስቦች መለወጥ ዋነኛ ምክንያቱ ተመልሶ ከአመራር *ሥርዓቱ ጋር* ይያያዛል፡፡ ለሱኒዎች ማንኛውም *ታማኝ* የሆነ ሰው *የሀዲስ* አስተላላፊ ሊሆን ቢችልም ለሺዓዎች ደግሞ አንድ *ሀዲስ* ተዓማኒ የሚሆነውና ተቀባይነት የሚያገኘው በታወቁ ኢማሞች አማካይነት የተላለፈ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ያም ሆኖ የሱኒና የሺዒ *የሀዲስ* ስብስቦች የዘገባ ሰንሰለት ልዩነት እንጂ በአብዛኛው የይዘት አንድነት ያላቸው ናቸው፡፡ ለዚህም አብነት የሚሆነው አስተላላፊዎቻቸው የተለያዩ ግለሰቦች ሆነው አንድ አይነት መልዕክት ያላቸው *ሀዲሶች* በሱኒና በሺዒ *የሀዲስ* ጥንቅሮች ውስጥ ተካተው የሚገኙ መሆኑ ነው፡፡[101]

በሸሪዓ የሕግ አቀራረብ ዘዴዎችና የአስረጂነት ጉዳዮች ላይ በሱኒና በሺዒ *መዝሓቦች* መካከል ያለው ልዩነት ከላይ እንደተዳሰሰው ሆኖ ከሕግ ይዘት አኳያ ያላቸውን ልዩነት ደግሞ በጥቅሉ እንመልከት፡፡ በአተረጓጎም ልዩነት የተነሳ የተለያየ *የፊቅሕ* ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ምክንያት በሱኒና በሺዓ *መዝሓቦች* መካከል ያለው ልዩነት በየትኛውም *መዝሓቦች* መካከል እንደሚኖር *የፊቅሕ* ልዩነት እንጂ ሱኒና ሺዒ ከመሆን ጋር የተያያዘ አይደለም፡፡[102] ስለሆነም *በፊቅሕ ረገድ* ያለ *የሁክም አሽ-ሸሪዒ* (ብይን) ልዩነት እንጂ የሱኒ-ሺዓ ልዩነት ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በሁለቱ የሙስሊም ክፍሎች መካከል ያለው *መሠረታዊ* ልዩነት የፖለቲካ አመራሮች የሚመረጡበት መስፈርት በመሆኑ ሌሎች እንደ ልዩነት የሚነሱ ነጥቦች ከዚህ *መሠረታዊ* ልዩነት የመነጩ መሆን ይገባቸዋል፡፡

ፕሮፌሰር ከማሊ ‹Sharia Law: An Introduction› በተሰኘው *መጽሐፋቸው* በግልና በቤተሰብ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉ የሱኒና የሺዓ ሕግ ልዩነቶቸን በአጭሩ ካብራሩበት ክፍል[103] መረዳት እንደሚቻለው በሱኒና በሺዓ *የሀዲስ* ስብስቦች መካከል ሰፊ የይዘት ልዩነት አይታይም፡፡ ስለሆነም *የፊቅሕ* ልዩነቶች በቁርአንና *በሱናሕ* አተረጓጎም ወይም *የኡሱል* ልዩነት ምክንያት የመጣ እንጂ ከሁለቱ የሙስሊም ማሕበረሰቦች የፖለቲካ እሳቤ የመነጨ ልዩነት አይደለም፡፡ በሌላ አገላለጽ የሁለቱ ልዩነት በሱኒ *መዝሓቦች* መካከል እንዳለ ልዩነት ሊታይ ይገባል፡፡ ይህ የእሳቤ ብዝኃነት እንደ ጊዜውና ተጨባጭ ሁኔታዉ ተስማሚ የሕግ አማራጮችን የሚያቀርብ ሰፊ የሕግ ማዕቀፍ እንደሆነ ተደርጎ መታየት ይገባዋል፡፡[104] ብዙኃኑ እንደሚያስበው ይህ ልዩነት በወገንተኝነት ስሜት ጽንፍ የሚያዝበት ሳይሆን ሸሪዓ ነባራዊ ሁኔታውን የሚያገናዝብና ተለዋዋጭ መሆን ይችል ዘንድ የሕግ ምርጫ ለማድረግ *(ተኽዪር)* የሚያመችና አንዱ ከሌላው የሚማርበት ምሁራዊ አሻራ እንጂ[105] በስፋት እንደሚናፈሰው አንዱ ሌላውን የማይከተል በራሱ እይታ ብቻ ታስሮ የሚኖርበት የጭፍንነትና የቡድናዊነት አመለካከት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ይገነዘቧል፡፡[106]

በሱኒ *መዝሓቦች* መካከል ያሉትን አማራጭ *የፊቅሕ* እሳቤዎችን ብቻ ሳይሆን የሺዓ መዝሓቦችንም ያማከለ ኢስላማዊ *የፊቅሕ* ግንዛቤና የሕግ አወጣጥ *ሥነ-ሥርዓት* በዘመኑ የሸሪዓ ምሁራን አትኩሮትን እያገኘ ያለና በጥቂት የሙስሊም ሃገራት የሕግ አወጣጥ ላይ ተግባራዊ የተደረገ ሚዛናዊ የሕግ

---

[100] ዝኒ ከማሁ ገጽ 90.
[101] ዝኒ ከማሁ.
[102] ዝኒ ከማሁ ገጽ 92.
[103] በጋብቻ አፈጻጸም በውርስ በእናትነትና በአባትነት አወሳሰንና በሌሎች ተመሳሳይ የቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ያሉ የሺዓና የሱኒ *የፊቅሕ* ሕግጋት ልዩነቶችን በተመለከተ የከማሊ (KAMALI, SHARIA LAW, *supra* note 7, pp. 90-92 ይመለከቷል፡፡)
[104] ዝኒ ከማሁ ገጽ 92.
[105] ዝኒ ከማሁ ገጽ 94-95, 275-276.
[106] ዝኒ ከማሁ ገጽ 92.

*ሥልጣኔ* ነው፡፡[107] *ይህ ኡሱልን መሠረት ያደረገ ፊቅሓዊ ምርጫ* ለወቅታዊ ችግሮች ተስማሚ የሆነ ሸሪዓዊ *መፍትሔዎችን* ከማስገኘቱም በተጨማሪ በሱኒና በሺዓ *መካከል ያለውን* ለዘመናት ክብደት የተሰጠውን *መሠረት-የለሽ* ልዩነት የሚያጠብና በእምነት ላይ ለተመሠረተና ብዝኃነት ለተከበረበት የአንድነት ምዕራፍ በር የሚከፍት ነው፡፡[108]

### መ. በመዝሓቦች መካከል ያሉ ጠቅላላ የልዩነት ምክንያቶች

በመዝሓቦች *መካከል ያለው* ልዩነት ከሕግ ጉዳዮች ተሻግሮ የእምነት ጉዳዮችንም የሚመለከትባቸው አጋጣሚዎቸ ቢኖሩም *የመዝሓብ* ልዩነት ከተባለ በትርጓሜው የሕግ አረዳድ ልዩነቶችን የሚያመለከት ነው፡፡[109] *የመዝሓብ* ልዩነቶች በአራት ጥቅል ምክንያቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ይኸውም በቁርአን አናቅጽ አተረጓጎም፣ በ*ሀዲስ* የተዓማኒነት ምዘናና አተረጓጎም፣ በ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎችና የአቀራረብ ዘዴዎችና በ*ኢጅቲሓድ* በሚደርሱባቸው *ፊቅሕ* ላይ በሚኖሩ ልዩነቶች ሊሆን ይችላል፡፡[110]

የቁርአን አተረጓጎምን በተመለከተ የአንቀጾች *መሻር* ላይ በሚኖር የአረዳድ ልዩነት ወይም በ*ሀዲስና* ቁርአን መካከል ሊኖር በሚችል የመሻር ግንኙነት ላይ ባለ የአስተያየት ልዩነት ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአሽ-ሻፊዒ *የነስኽ* እሳቤ ቁርአን በቁርአን ወይም *ሱናሕ* በ*ሱናሕ* ሊሻር የሚችልበትን *የነስኽ ግንኙነት* የሚቀበሉ ሲሆን ሌሎች *መዝሓቦች* ደግሞ አንዱ ሌላውን ሊሽር እንደሚችል *ያምናሉ*፡፡[111] በተጨማሪም የቁርአን አንቀፆች ጥቅልና ልዩ በሚል ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ የሕግ ሊቃውንት *የዐም* እና *የኻስ* ትርጓሜና አንድምታ ላይ የተለያየ ድምዳሜ ላይ የደረሱ መሆኑ ሌላው የልዩነቱ መንስኤ ነው፡፡[112]

በ*ሱናሕ* ላይ ያለው ልዩነት የአተረጓጎም ብቻ ሳይሆን ለ*ሀዲሶች* ከሚሰጠው የተለያየ የተዓማኒነት ምዘናና የአስረጅነት ደረጃ የሚመጣ ነው፡፡ *ሀነፊዎችና ሻፊዒዎች* ጥብቅ የሆኑ የምዘና መስፈርቶችን ሲከተሉ *ማሊኪዎችና ሀንበሊዎች* ደግሞ ልዝብ አቋም አላቸው፡፡ ለምሳሌ በአንድ አስተላላፊ ብቻ የተላለፈን ነጠላ *ሀዲስ* አሽ-ሻፊዒና ኢብን-ሀንበል በቀጥታ የሚቀበሉት ሲሆን አቡ-ሀኒፋና ማሊክ ደግሞ የተወሰኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን የሚያሟላ ከሆነ ይቀበሉታል፡፡ በተጨማሪም በ*ሀዲሶች* መካከል መሻር ካጋጠመ እነዚህን ጉዳዮች የሚፈቱባቸው የአተረጓጎም ዘዴዎች የተለያዩ ይሆናሉ፡፡ *ሙተዋቲር ሀዲስ* (በብዙ አስተላላፊዎችና የዘገባ ሰንሰለቶች የተዘገበ*)* በነጠላ *ሀዲስ* ሊሻር የማይችል መሆኑ የብዙኃኑ አቋም ቢሆንም *ሀነፊዎች* ደግሞ *አሀድ ሀዲስ ሙተዋቲሩን* ሊሽር ይችላል የሚል አቀራረብ አላቸው፡፡[113]

በ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች ላይ ባለ *የመዝሓቦች* ልዩነት ምክንያት *የፊቅሕ* ድምዳሜ ልዩነቶች እንዳሉ ቀደም ባሉት *የመዛሒብ* ርዕሶች ሥር ተብራርቷል፡፡ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ ለመስጠት ያህል *ሀነፊዎች ቂያስን* ተፈፃሚ ማድረግ ያልተፈለገ/አስከፊ ውጤትን የሚያስከትል በሚሆን ጊዜ ርትዕ ተፈፃሚ ሲያደርጉ ማሊኪዎች ደግሞ የሕዝብ ጥቅም ተግባራዊ ያደርጋሉ:: ሁለቱ በዋናነት ተመሳሳይ ቢሆንም በአንዳንድ ዝርዝር ነጥቦች ላይ ልዩነት አላቸው፡፡[114] አሽ-ሻፊዒ እነዚህን *የሀነፊና የማሊኪ* የሕግ መርሆዎች ግልጽ ሸሪዓዊ *መሠረት* የሌላቸውና በግል እሳቤ ላይ የተገነቡ ዘፈቀዳዊ ጣልቃ-ገብነቶች

---

[107] ዝኒ ከማሁ ገጽ 272-273.
[108] ዝኒ ከማሁ ገጽ 92.
[109] KAMALI, SHARIA LAW, *ግርጌ ማስታወሻ* 7, p. 93.
[110] ዝኒ ከማሁ.
[111] ዝኒ ከማሁ.
[112] ዝኒ ከማሁ.
[113] ዝኒ ከማሁ ገጽ pp. 93-94.
[114] ዝኒ ከማሁ ገጽ 94.

ናቸው በሚል ሁለቱንም አይቀበሉም፡፡[115] ሻፌዒዎች ሀንበሊዎችና ባለ አስራ-ሁለትዮሽ ሺዓዎች ኢስቲስሃብ (ነባሩ ይቀጥላል- የቀጣይነት ግምት) የተሰኘውን የሸሪዓ ሕግ ንድፈ-ሐሳብ ይቀበላሉ፡፡[116]

### ሠ. መዝሓቦች በኢትዮጵያ

የሸሪዓ ት/ቤቶች በኢትየጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ ውስጥ ከነበረዉ የእድገት ታሪክ በተጨማሪ ባጠቃላይ ከ19ኛው ም.ል መጨረሻ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ኢስላምና ሙስሊሞች የሥልጣኔ አሻራን በተመለከተ በዘርፉ የታሪክ ምሁራን እጅ የሚገኙ የታሪክ ምንጮች እጅግ አናሳ በመሆናቸው[117] እንደሌላው የኢትዮጵያ ቀደምት ሙስሊም ማህበረሰብ ልዩ ልዩ የታሪክ ዘውጎች ሁሉ በትምህርትና በእውቀት ባህላቸው ላይ ያሉት መረጃዎች ውስንና አሻሚ ድምዳሜዎች ላይ የሚያደርሱ ናቸው፡፡ መዝሓባዊ የፊቅሕ ትምህርት በ16ኛው ም.ል በሐረር ከተማ ይሰጥ እንደነበረና ይህ የእውቀት አሻራ የመን ይገኙ ከነበሩ ዑለማእ የተገኘ እንደሆነ ታዋቂው ‹የኢስላም በኢትዮጵያ› አጥኚ ትርሚንግሓም ይገልጻል፡፡[118] እንደ ሁሴን አህመድ ገለጻ ደግሞ የፊቅሕ እውቀት በኢትዮጵያ የተጀመረው ሰፊ ትምህርታዊ አቀራረብና ማህበረሰባዊ ተደራሽነት ላይኖረው ቢችልም ከ12ኛው ም.ል ጀምሮ በኢፋት ይኖሩ ከነበሩ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማሕበረሰብ ውስጥ የሻፊዒ መዝሓብ ይታወቅ የነበረ መሆኑን ሥነ-ቃላዊ መረጃዎችን በማጣቀስ ያስረዳል፡፡[119] ይህ በእንዲህ እንዳለ በ19ኛው መቶ ክ/ዘመን በወሎና ኢፋት የነበረው የሙስሊም ትምህርት ንቅናቄ መሠረቱን ያገኘው በ15ኛው ም.ል መጨረሻ ጀምሮ በሐረር ከተዋወቀው የፊቅሕ ትምህርት ነው፡፡[120]

በ14ኛው መቶ ክ/ዘመን በሐረር ይታወቁ የነበሩት መዝሓቦች ሻፊዒና ሀነፊ እንደሆኑ ትሪሚንግሓም ገልጿል፡፡ ይህ የእውቀት ጥንስስ በጊዜ ሒደት ከወሎ ከይፋት ከጎንደር ይመጡ በነበሩ ተማሪዎች አማካይነት ወደ መሐል ኢትዮጵያና ወሎ ገብቶ በተለያዩ ሃገር-በቀል የሱፊያ ማዕከላት (ዛውያዎች) በኩል ሰፊ ትኩረትንና ሥርጭት ሊያገኝ ችሏል፡፡ የሻፊዒና የሀነፊ መዝሓቦች ብቻ በኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ የትምህርት ባህል አካል ለመሆን የቻሉ ሲሆን የማሊኪ መዝሓብ በሃገሪቱ ሱዳን አዋሳኝ ሥፍራዎች በሚገኙ ሙስሊም ማህበረሰቦች ዘንድ ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ እጅግ አናሳ ሥርጭትና እውቅና ያለው ነው፡፡[121] የሀንበሊ መዝሓብ በሕግ አረዳድ ዘዴው ጥብቅ በመሆኑና የሃገሪቱ ሙስሊሞች ከሌሎች የእምነት ማህበረሰቦች ጋር ካላቸው ዘርፈ-ብዙ መስተጋብርና ተለማጭ ሃይማኖታዊ እሴቶች ጋር የሚጣጣም ባለመሆኑ መዝሓቡ በአንዳንድ ግለሰቦች በኩል ከሚንጸባረቀው በዘለለ ሰፊ ተቀባይነትና የሙስሊም ትምህርት አካል ለመሆን አልቻለም፡፡[122] የሻፊዒ መዝሓብ የመንን መሠረት አድርጎ በጠቅላላው በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ሰፊ የሥርጭት እውነታን በተከተለ አኳኋን በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ዘንድም ቢሆን ከሀነፊ መዝሓብ ጋር በማይነጻጸር ደረጃ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሙስሊም የፊቅሕ ትምህርት ባህል ለመያዝ ችሏል፡፡[123] የሀነፊ መዝሓብ አሁንም በሐረር የነበረውን

---

[115] ዝኒ ከማሁ.

[116] ዝኒ ከማሁ.

[117] HUSSEIN AHMED, ISLAM IN NINETEENTH CENTURY WALLO, ETHIOPIA, REVIVAL, REFORM AND REACTION, 75 (Brill, Lieden, 2000).

[118] J. SPENCER TRIMINGHAM, ISLAM IN ETHIOPIA, 234 (Frank Cass & Co., London, 1965).

[119] Hussein, ግርጌ ማስታወሻ 101, p. 65.

[120] Hussein Ahmed, *Harar-Wallo Relations Revisited: Historical, Religious and Cultural Dimensions*, AFRICAN STUDY MONOGRAPHS, Suppl.41, 2010 pp. 112-113.

[121] Hussein, ግርጌ ማስታወሻ 115, p. 66.

[122] ዝኒ ከማሁ ገጽ 66.

[123] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 65-66፡፡ የሺዓ መዝሓቦች በኢትዮጵያ ሙስሊም ሕብረተሰብ የፊቅሕ እውቀት አሻራ ውስጥ ያለውን ድርሻ በተመለከተ ከደቡብ አረቢያ ፈልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የሺዓ እሳቤ የሚያራምዱ ጥቂት ዘይዲዎችና ዒባዲዎች እንዳሉ ዛኪ ሙስጠፋ የገለጸውን በማጠቀስ እነዚህ ሺዓ ሙስሊም ማህበረሰቦች ራሳቸውን እንደ ሺዓ የማያቀርቡ ቢሆንም ሃይማኖታዊ ተግባራቸው ሺዓዊ የሆነ ሙስሊሞች ይገኛሉ በማለት ሙሀመድ አብዶ ገልጿል፡፡

*ትምህርታዊ እውቅና ተከትሎ በወሎ በስፋት የሚጠና ሲሆን በጎጃም በጅማና ሐረርም ብዙ ተከታዮች አሉት፡፡*[124]

*ይህ መዝሓባዊ የፊቅሕ ብዝሓነት በሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሸሪዓ አተረጓጎም ላይ አዎንታዊና አሉታዊ ውጤቶች ሊኖሩት እንደሚችል ሙሀመድ አብዶ ሲገልጽ በግልና ቤተሰባዊ ጉዳዮች ላይ በሊቃውንቱ መካከል ያለው የአተረጓጎም ልዩነት ፍ/ቤቶቹ የሙስሊሙን ማሕበረሰብ ነባራዊ እውነታዎችና ለፍ/ቤቶቹ የሚቀርቡ ልዩ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ተለማጭ የሸሪዓ አረዳድ ለመያዝ የሚያስችል ሲሆን በሌላ በኩል ልዩነቶቹ በሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚሰሩ ዳኞች ለፍ/ቤቶቹ በሚቀርቡ ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች የተለያዩ እንዲሆኑ በማድረግ ወጥነት የጎደለውና ተገማች ያልሆነ የፍርድ ሥርዓትን የሚፈጥር እንደሆነ ይጠቁማል፡፡*[125] *ለዚህ እንደ መፍትሔ ያመለከተው በሥነ-ሥርዓት ጉዳዮች ላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የፍትሐ-ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን እንዲተገብሩ በመደረጉ የተፈጠረውን ወጥ የሥነ-ሥርዓት አካሄድን በመከተል በግልና በቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ የሚደረገውን የሸሪዓ ሕግ ክፍል በማጥናት መዝሓባዊ የአቋም ልዩነቶችን ሃገራዊና ማሕበረሰባዊ እውነታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም እንደ ጉዳዩ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነውን የዳኝነት የተለማጭነት ደረጃን በመጠበቅ ወጥ የሸሪዓ የግልና የቤተሰብ ሕግ ጥንቅር* (Codified Islamic Personal and Family Law) *ቢዘጋጅ አሉታዊ ገጽታውን መቀነስ ይቻላል፡፡*[126]

## *ረ. ማጠቃለያ*

*የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት የሕግ ብዝኃነትን የሚያረጋግጡ አንቀጾችን ሲያካትት በሃገሪቱ የሚገኙ ባህልና ሃይማኖትን የሚከተሉ ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች በሃይማኖትና በባህል ሕጎች የመዳኘት ፍላጎታቸዉን ለማሟላት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መደበኛውን የፍትሕ ሥርዓት ከማገዝ አንጻር በግጭት አፈታት ሥርዓታቸው ካላቸው ጤታማነት ለመጠቀም ይቻል ዘንድ እዉቅናና የተፈጻሚነት ድርሻ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተዘረጋው ሕገ-መንግሥታዊ እድል እየተጠቀመ ያለ መደበኛ ያልሆነ የዳኝነት አካል ቢኖር የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ብቻ ናቸው፡፡*

*የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የግልና ቤተሰብ ግጭቶችን ለመፍታት ተፈጻሚ የሚያደርጉት ሸሪዓን ስለሆነ የሸሪዓ ሕግ ከታሪካዊ እድገቱ በተጨማሪ አጠቃላይ የሕግ መርሆዎቹና ዝርዝር ሕጎች የሚጠኑበት የእውቀት መስኮችን መረዳት እንዲሁም የሸሪዓ ሕግ በኢትዮጵያ ዙሪያ ተፈጻሚ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ሃገራዊና ማህበረሰባዊ እውነታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አግባብነት ባላቸው የሸሪዓ ሕግ ዘርፎች ላይ ጥናት ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህም የሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሕግ አተረጓጎምና አተገባበር የሸሪዓ ዓላማዎችና ግቦች ማሳካት በሚችልበት ጎዳና ላይ እንዲራመድ ማድረግ ይችላል፡፡*

*በዚህ ጽሑፍ የኡሱል አል-ፊቅሕና ፊቅሕ ጥናቶች ታሪካዊ ዳራ የሆነውን የሸሪዓ ሕግ አነሳስ የመዝሓቦች አመሠራረት ለሸሪዓ የሕግ ፍልስፍና እና ዝርዝር ሕግጋት መዳበር ያላቸው ጉልህ*

---

(Muhammad, *supra* note 2, p. 90, f.n. 61). ነገር ግን ሱኒ እና ሺዓ ማህበረሰቦች ከመሠረታዊ የእምነት ቀኖና አንድነታቸው በተጨማሪ በሱፍያ መንፈሳዊ ሥርዓታቸው የተወራረሱባቸው በርካታ ሥርዓተ-እሴቶች የሚገኙ ከመሆኑ አኳያ በኢትዮጵያ አሉ የተባሉት ሺዓ ሙስሊሞች ከእነዚህ ሰፊ የጋራ እሴቶች መካከል በሸሪዓ ሕግ አቀራረባቸው የሺዓ መዝሓቦችን የሚከተሉ መሆኑ አልተገለጸም፡፡ ዛኪ እንደገለጸው በታሪክ ከአረቢያ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ሺዓዎች እንዳሉ የገለጸው ተዓማኒ ቢሆንም እንኳ በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ እውቀት በሸሪዓ አቀረራቡ የሺዓ መዝሓብ ተግባራዊ የሚያደርግ ሙስሊም ሕብረተሰብ በየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ አይገኝም፡፡ የሺዓ መዝሓባዊ ቅርጹም በኢትዮጵያ ሙስሊም የፊቅሕ እውቀት ማዕቀፍ ውስጥ አይታወቅም፡፡ (ዛኪ ሙስጠፋ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የእስላም ፍርድ ቤቶች የሚሰራበት ሕግ፤ ለሸሪዓ ሕግ በሥራ ላይ መዋል መቀጠል ምክንያት የሆኑ ነገሮች፣ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት፣ ቅጽ 9፣ ቁጥር 1፣ 1965፣ ገጽ 143 ይመለከቷል፡፡).

[124] ዝኒ ከማሁ ገጽ 66.

[125] Muhammad, *supra* note 2, p. 90

[126] Muhammad, *supra* note 2, p. 90

አስተዋጽኦዎች አጠቃላይ ዳሰሳ ቀርቧል፡፡ በዘመኑ የሸሪዓ እድገት አስተሳሰብ መዝሓቦችን በጭፍን ከመከተል ይልቅ ከሕብረተሰቡ የእድገት ደረጃና ተጨባጭ ችግሮች አኳያ ሸሪዓ ተለማጭ መሆን ይችል ዘንድ ከምክንያታዊ አስተሳሰብና ርትዕ ጋር ተስማሚ የሆነውን *የመዝሓብና የፉቅሓእ* የሕግ መርሆዎችና ድንጋጌ ለመምረጥ አመቺ የሆነ የሸሪዓ ብዝኃነት ማዕቀፍ ተደረጎ መወሰድ እንዳለበት እንደ ጧሃ ጃቢር ዐልዋኒ ያሉ ዘመነኛ *የኡሱል ምሁራን* ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም *መዝሓቦችና* ቀደምት የሕግ ሊቃውንት የያዟቸው የሕግ አስተያየቶች ለአጠቃላይ የዓለም ሙስሊምም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝበ-ሙስሊም ማህበረሰባዊ *ሥ*ልጣኔና አስተሳሰብ *ጋ*ር የማይጣጣምና ሸሪዓዊ የፍትሕና የልማት ዓላማዎችን የማያሳካ ከሆነ ነባራዊ እውነታውን መሠረት ያደረገ አዲስ የሸሪዓ ምርምር በማድረግ በነባሩ *የፊቅሕ* ሕግ ላይ አስፈላጊውን ማሻሻያና ለውጥ ማድረግ የሚገባ መሆኑን በአጽንኦት ያስረዳሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሸሪዓ ፍ/ቤቶችም ቢሆኑ የግልና የቤተሰብ ሕጎችን ተፈጻሚ በማድረግ ሂደት ላይ የመዝሓቦችን ተጓዳኝና ተነጻጻሪ አቋሞች *ለተኸይር* (አማራጭ የሐሳብ ምንጭ) መጠቀም እንዳለባቸው እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ *መቃሲድንና* የአካባቢውን ማህበረሰብ ታሳቢ ያደረጉ አዲስ *የፊቅሕ* እይታዎችን ማዳበር ይኖርባቸዋል፡፡ በሃገሪቱ ያለው የሕግ ትምህርትና ምርምር አካላት ምሁራንና ተማሪዎች በበኩላቸው ሸሪዓ በሃገሪቱ ዜጎች ላይ ተፈጻሚ በሆነበት መጠን ለትክክለኛ ትግበራውና ውጤታማነቱ አግባብነት ያላቸውና አስፈላጊ የሆኑ *የኡሱል አል-ፊቅሕና የፊቅሕ* ሕግ ርዕሶችን ከሸሪዓ ፍ/ቤቶች አሰራርና ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ጋር በማዛመድ ጥናት ማድረግና ለውጤቱ ምትራዊ አስተዋጽኦ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

* * * * *